# የንባብ ልምድ ቅኝት - በአዲስ አበባ

□ረ□ □በሬ*

*አጠቃሎ፡- የዚህ ቅኝት ዋና ዓላማ የንባብ ልምድን ይዞታ (በአዲስ አበባ) መመርመር ነው። በውስጡም በት/ቤቶች ስለሚገኘው መሠረታዊ የንባብ ልምምድ፣ ከት/ቤት ውጪ ስላለው ሁኔታ፣ ስለሚነበቡት መጻሕፍት ዓይነትና አገኛኘት፣ ስለደጋፊና አደናቃፊ ሁኔታዎቹ፣ የሚያነሱ ዝርዝር ጥያቄዎች ተካትተዋል። ስለንባብ ምንነትና ስለ ልምዱ መዳበርም ልዩ ልዩ ሰነዶች በክለሳ ድርሳኑ ውስጥ ተመርምረዋል፤ በሱም መሠረት 14 ከፊል ክፍትና ዝግ ጥያቄዎች የያዘ መጠይቅ ተሰናድቶ ለመቶ ሰዎች ተሰራጭቷል። ከመቶዎቹ መጠይቆች 74ቱ ተመልሰዋል። ከመጠይቁ የተገኘው መረጃም በገላጭ የምርምር ስልት ተደራጅቶና ተከፋፍሎ ተተንትኗል። በትንታኔው መሠረት የተገኘው ውጤት የሚያመለክተው በመላሾቹ ማንጠሪያነት ሲታይ፣ በአዲስ አበባ ያለው የንባብ ልምድ ያልዳበረ መሆኑን እና ተጨማሪ ዝርዝር ጥናት በማካሄድ የችግሩን ስፋትና ጥልቀት በሚገባ መርምሮና ደረጃውን ተገንዝቦ የሚቃለልበትን ስልት መቀየስ ያስፈልጋል የሚል ነው።*

## የጥናቱ ዳራ

በተለያዩ መደበኛና ኢመደበኛ አጋጣሚዎች ሁሉ ስለንባብ ልምዳችን ሲወሳ የሚሰጡት አስተያየቶችና፣ የሚቀርቡት ድምዳሜዎች እጅጉን አሉታዊና ተስፋ አስቆራጮች ናቸው ማለት ይቻላል። አብዛኞቹ አስተያየቶች መነሻቸው በቂ ጥናት ሳይሆን ነሲባዊ አስተሳሰብ፣ ግምታዊ ምደባ፣ ከፊል ምርምራዊ ማጠቃለያ ናቸው ማለትም ያስኬዳል። አስተያየቶቹም የሚቀርቡት ልዩ ልዩ ልምድ፣ እውቀትና ሙያ ካላቸው ግለሰቦች ወይም እንደቡድን በሚታሰቡ አካሎች ጭምር ነው።[1] በተለይ

---

* በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት መምህር፣ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

[1] ደረጀ ደስታ 1986 በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ግንቦት 21 ቀን በ54ኛ ዓመት ቁ. 220ኛ እትሙ እለተ ሰንበት አምድ በገጽ 2 ላይ ‹‹መጽሐፍ ያልያዘ ትውልድ›› በሚል ርእስ የወቅቱን የኩራዝ አሳታሚ ድርጅትን ኃላፊዎች አነጋግሮ ነበር፤ በ1988 ደግሞ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጋዜጣ ኅዳር 27-ታህሳስ 3 በ6ኛ ዓመት ቁ. 140ኛ እትሙ በገጽ 7 ላይ ‹‹የዘመናችን የህትመት ሁኔታ ሲቃኝ›› በሚል ርእስ ደራሲዎች አሳታሚዎችና አከፋፋዮች የተወያዩበት ዘገባ ቀርቧል። በሁለቱም ጋዜጦች ላይ አንባቢ ጨርሶ ጠፍቷል የሚል ሀሳብ አልቀረበም፤ ይሁን እንጂ መጻሕፍትን በሚፈለገው ዓይነት፣ መጠንና ጥራት ለማቅረብ ልዩ ልዩ ችግሮች እንዳሉ በስፋት ተዘግቧል። በሚያዝያ 1999 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርና የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ድርጅት በጋራ ባዘጋጁትና በርካታ ሰዎች በተሳተፉበት ውይይት የንባብ ባህላችን ልዩ ልዩ ችግሮች እንዳሉበት ተወስቷል።

በየአጋጣሚው በምናዳምጣቸውና በምንመለከታቸው የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ዘዴዎችና በምናነባቸው ልዩ ልዩ የኅትመት ውጤቶች ዘወትር የሚያጋጥመን ማጠቃለያ ኢትዮጵያውያን የንባብ ልምድ የለንም የሚል ነው፡፡ እንዲሁም ልዩ ልዩ መጻሕፍትና ትምህርት ተኮር ጉባኤዎች ወይም ውይይቶች የሚከናወኑባቸው መድረኮች ሲዘጋጁ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የንባብ ነገር ከተነሳ ኢትዮጵያውያን የንባብ ባህላችን አልዳበረም የሚል ማጠቃለያ ሲሰጥ መስማት ልማድ ሆኖ ቆይቷል፤ ለምሳሌ ያህልም አያልነህ ‹‹ግልጽና እውቅ በሆኑ አያሌ ምክንያቶች የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ለረጅም ጊዜ ቀጭጮ ቆይቷል፡፡ ሕዝቡም በማይምነት መጋረጃ ውስጥ ተሸፍኖ የቆየ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የንባብ ባህሉ አልዳበረም›› (አያልነህ፤ 1985፣ ገጽ 2) ሲል ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም፣

> … ስለየዘመኑ እለታዊ ኑሮ ተርታው ሰው በሚገባው ቋንቋ የተፃፉ፣ ፊደል የቆጠረ ሰው ስለራሱ ህይወት እያነበበ የማንበብ ልምዱን እንዲያዳብር የሚያግዙ ፅሁፎች እምብዛም አልነበሩም፡፡ በዚህ ላይ የማንበብና የመፃፍ ትምህርት እንኳን ጥንት ዛሬም በወጉ አልተስፋፋም፡፡ ስለዚህ እንኳን በጥንቱ የኢትዮጵያ ቤተሰብ ቀርቶ በዛሬው ቤተሰብም የማንበብ ልምድ አለ ለማለት ጨርሶ አይቻልም (ፈቃደ፤ 1997፣ ገጽ 5)፡፡

በማለት ከላይ የቀረበውን መንደርደሪያ ሀሳብ ያጠናክራል፡፡ ቀደም ሲልም በ Tamene (1992) በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የትርፍ ጊዜ ንባብ ልምድ ላይ የቀረበው ጥናትም የደረሰበት ማጠቃለያ በተማሪዎች ዘንድ ያለው የንባብ ልምድ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ያስረዳል፡፡ እንዲሁም ዓለም እሸቱ በአዲስ አበባ ወጣቶች መነሻነት ባደረገው የንባብ ልምድ ዳሰሳ ወጣቶቹ የንባብን አስፈላጊነት የሚያምኑ ቢሆኑም ያላቸው ልምድ ግን ዝቅተኛ መሆኑን እንደሚከተለው ገልጾአል ፡፡

> … አብዛኞቹ ወጣቶች ለንባብ ከፍተኛ ግምት ይሰጣሉ፡፡ የንባብ ልምድም ሊዳብርና ሊያድግ የሚገባው ጉዳይ መሆኑን ያምናሉ፡፡ ይሁን እንጂ የብዙዎቹ የንባብ ልምድ የሚያመረቃ አይደለም፡፡ ከመጻሕፍት ጋርም ያላቸው ትስስርም የላላ ነው (አለም፤ 2001፤ ገጽ 78)፡፡

በሌላ በኩል ከላይ ከቀረቡት በተለየ ሁኔታ (Birhanu, 1999) ባደረው ጥናት ደግሞ በባህር ዳር ከተማ የሚኖሩ በትምህርት ደረጃቸው 12ኛና ከዚያ በላይ የሆኑ ግለሰቦች (97% የሚሆኑት) አብዛኛውን ትርፍ ጊዜያቸውን በማንበብ እንደሚያሳልፉ አረጋግጧል፡፡ እነዚህ ተጠኚዎች መጻሕፍትን አንባቢዎች ብቻ ሳይሆኑ ገዢዎችም መሆናቸውን ከብርሃኑ ጥናት ለመረዳ ተችሏል፡፡

ይሁንና ከብርሃኑ በተጻራሪ በተለምዶ ባካበቱት ተመክሮና ምልከታ ላይ ተንተርሰው ስለንባብ ልምድ ሀሳብ የሚሰነዝሩ ተናጋሪዎችም ሆኑ ጥናት አቅራቢዎች አጠንክረው የሚገልጹት በንባብ ባህላችን ላይ ችግር እንዳለ ነው፡፡

የንባብ ባህልንና ልምድን ርእሰ ጉዳያቸው ባደረጉና በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ምእመናን ላይ በተደረጉ ጥናቶችም (ምሕረቱ፤ 1999፣ Concher, 1970) እንዲሁ የንባብ ባህል እንደሚፈለገውና መሆን እንደሚገባው ያደገ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በሌላም በኩል፣ በተለያዩ ጊዜያት የንባብ ልምድ በሚጀመርባቸውና በሚጎለብትባቸው የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የእለት ተእለት የክፍል ውስጥ ክንዋኔው፣ በማስተማሪያ ቁሳቁሶቹና በትምህርት ማቅረቢያ ስልቶቹ ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የንባብ ልምድን ለማስገኘት የሚያስፈልጉት ቀዳሚ ተግባራት በወጉ ያልተከናወኑ መሆናቸውን ነው (ንጉሥ፤ 1993፣ ጋሻው፤ 1995፣ ታዬ፤ 1997)፡፡ እነዚህ ጥናቶች በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች የተደረጉ በመሆናቸው ስለንባብ ትምህርት አሰጣጥ ጉድለት ጠቋሚ መረጃ ይገኝባቸዋል፡፡ አቅማቸውና የጥናት ገደባቸው በፈቀደ መጠንም የትምህርት አቀራረቡና የማስተማሪያ ቁሳቁሶቹ የሚሻሻሉባቸውን የመፍትሄ ሀሳቦች ሰንዝረዋል:: በመሆኑም የንባብ ልምዳችን ጉዳይ በምርምር የተደገፈ ተከታታይ ፍተሻ የሚያስፈልገው ውለኛ ርእሰ ጉዳይ ሆኖ ይታያል፡፡ በዚህም የተነሳ ‹‹የንባብ ልምድ የለንም›› የሚለውንም ሆነ ‹‹የንባብ ልምዳችን አልዳበረም›› የሚለውን ሀሳብ መመርመርና የወቅቱን ተጨባጭ እውነት መገንዘብ የትምህርት ሥራ የሚያሳስባቸውን ወገኖች ሁሉ የሚጎነትል ነገር ነው፡፡ ይህም ቅኝት የተደረገው ከላይ በአዎንታዊነትም ሆነ በአሉታዊነት የቀረቡትን ሀሳቦች በተለየ ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ ውስጥ በማስገባት መርምሮ በአካባቢያችን ስላለው የንባብ ልምድና ደረጃ ሰፋ ያለ ጥናት ለማካሄድ እንዲቻል የመነሻ ሀሳብ ለማግኘት ነው፡፡

## የቅኝቱ ዓላማና ዝርዝር ጥያቄዎች

የዚህ ቅኝት ዋና ዓላማ የንባብ ልምድንና የሚገለጽበትን ሁኔታ መመርመር ነው። በዝርዝር ሲተነተን የሚከተሉት የምርምር ጥያቄዎች አሉት፤

- መላሾች በትምህርት ቤት ያገኙት የንባብ ልምድ ምን ይመስላል?
- ከመደበኛ ትምህርት ቤት ውጪ (በሥራ ዓለም፣ በእለት ተእለት ኑሮና ውሎ ውስጥ) ያላቸው የንባብ ልምድ እንዴት ይገለጻል?
- ምን ምን ዓይነት መጻሕፍት፣ ለምን ዓላማ ያነባሉ?
- የሚያነቧቸውን መጻሕፍት ከየትና እንዴት ያገኛሉ?
- የንባብን ልምድ የሚደግፉና የሚያደናቅፉ ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው?
- በንባብ ልምድ ይበልጥ ተጠቃሚ ለመሆን ምን ቢደረግ ይሻላል? የሚሉ ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎች ናቸው።

## የመረጃ አሰባሰብ

የንባብ ልምድ ቅኝቱ የተካሄደው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ ሰዎችን የጽሑፍ መጠይቅ በማስሞላት ነው። ሰዎቹ የተመረጡት በአጋጣሚ ናሙና አወሳሰድ ዘዴ ሲሆን ቦታዎቹም አራት ኪሎ፣ ፒያሳ፣ ለም ሆቴልና ብሔራዊ ትያትር አካባቢ በሚገኙ የህዝብ መዝናኛ ሬስቶራንቶችና ቡና ቤቶች፣ ሻይ ቡና ለማለት ድንገት ካጋጠሙ ግለሰቦች፤ በሾላ፣ በላምበረትና በገርጂ አካባቢ ባሉ የመኖሪያ ሰፈሮች ከሚኖሩ ሰዎች በመስከረም 2001 ዓ.ም. ነው። ከነዚህ ግለሰቦች የተሰበሰበው መረጃ የተተነተነው በገላጭ የምርምር ዘዴ ሲሆን የተሰላውም በመቶኛ ብቻ ነው።[2]

## የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ የሚሸፍነው ከላይ በ1.3. ላይ እንደተጠቆመው፣ በልዩ ልዩ ሙያ መስክ የተሰማሩ፣ ልዩ ልዩ የትምህርትና የኃላፊነት ደረጃ ያላቸውና በተለያዩ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ከሆኑ ሰባ አራት ያህል ሰዎች ነው። እነዚህ ተጠኝዎች በከተማው

[2] መረጃ በመሰብሰብ ረገድ በተጠቀሱት አካባቢዎች ያሉ ወዳጆቼ ስለተባበሩኝ አጅግ አድርጌ አመሰግናቸዋለሁ።

ያለውን የንባብ ልምድ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ የሚወክሉ አይደሉም። ይሁንና በመኖሪያ ሠፈር፣ በመሥሪያ ቤት፣ በልምድና በትምህርት ረገድ የተለያዩ መሆናቸው ራሱ በርእሰ ጉዳዩ ላይ የሚፈነጥቀው እውነታ ይኖራል በሚል መነሻ ቅኝቱ ተካሂዷል።

## ክለሳ ድርሳናት

የዚህ ጽሑፍ መሠረታዊ ማጠንጠኛ የንባብን ልምድ መቃኘት ነው። በዚህ መሠረት በሌሎች አገሮችና አካባቢዎች የተደረጉ ጥናቶችን መፈተሽ እኛ ያለንበትን እውነታ በተገቢው መንገድ ለመረዳት ያግዛል። የግብፅን ጎልማሶች የንባብ ልምድ ለመቃኘት ሲል የሴኔጋልን የኮሌጅ ተማሪዎችና ጎልማሶች እንደማነጻጸሪያ በመጠቀም የተደረገ ጥናት የሚጠቁመው በሁለቱም አገሮች የንባብ ልምድ እሚጠበቅበት ደረጃ ላይ አለመድረሱን ነው ። በተጠቀሱት አገሮች የንባብ ልምድ እንዳይጎለብት የሚያደርጉ ምክንያቶችም ተጠቁመዋል። እነሱም የትምህርት አሰጣጡ በተራ ሸምደዳ ላይ ማተኮሩ፣ የመማሪያና የማንበቢያ ቋንቋ ተጽእኖ፣ በትምህርት ቤቶች በቂ ቤተ መጻሕፍት አለመኖራቸው፣ ተስማሚ የንባብ መለማመጃዎች አለመገኘት፣ የመጻሕፍት ዋጋ ውድነት በዋናነት የተነሱ ነጥቦች ናቸው። ለችግሩ መፍትሔ ተደርጎ የተጠቆመው ሀሳብም በትምህርት ቤቶች ውስጥ የንባብ ትምህርትን በሚገባ ማስተማር እንደሚስፈልግ፣ ለተጠቀሱትም ችግሮች ማቃለያ ዘዴ መቀየስ እንደሚገባ ነው (Zikri, 1986)። ከላይ የተጠቀሰውም የታመነ (Tamene, 1992) ጥናት የደረሰበት ግኝት በከፊል እዚህ ከተጠቀሱት ችግሮችና መፍትሔዎች ጋር ይጣጣማል ። ከዚህ ቀጥሎ የዚህ ቅኝት ዋነኛ ርዕሰ ጉዳይ ስለሆነው ስለ ንባብ ልምድ ምንነትና እንዴት ሊዳብር እንደሚችል መጠነኛ ማብራሪያ ይቀርባል።

## የንባብ ምንነትና ልምድ

ንባብ ሲነሳ አብሮ መጠቀስ ያለበት ክሂሉ እጅግ ግለኛ የመሆኑ ጉዳይ ነው። በቦታና በጊዜ ከራቀ ጸሐፊ የቀረበ መልእክትን ለመረዳትና ምላሽ ለመስጠት የሚደረግ ረቂቅ አእምሮታዊ (ግለኛ እሰጥ አገባ) ሂደት መሆኑ ባለሙያዎች ያስረዳሉ (Davies, 1995; Grellet, 1981; Reutzel, and Cooter, 1999; Ruddell, 1999)። የሚነበብን ጽሑፍ ምንነት ለመገንዘብ፣ በአንባቢው አእምሮ

ውስጥ ቀደም ሲል በነበሩ ልምዶችና ተመክሮዎች ላይ በመመሥረት የሚከናወን፣ የሚብሰለሰልና የሚውጠነጠን ከዚያም አንዳች ተግባቦታዊ ውሳኔ ላይ ለመድረስ የሚያስችል ጠቃሚ ክሂል ነው - የንባብ ክሂል። በመሆኑም፣ ንባብ በዝርዝር ሲታይ፣ ስለአንድ ርእሰ ጉዳይ ለማወቅ በሚያነሳሳ ፍላጎት ላይ የሚመረኮዝ፣ የሚነበበው ጽሑፍ በሚፈጥረው ስነውበታዊ ጉጉት ሳቢያ፣ ለንባብ በቀረበው ጽሑፍ ውስጥ በተነሱት ሀሳቦች ውስብስብነትና ተፈታታኝነት ምክንያት፣ ከንባብ ከሚገኘው ተጨባጭ ማበረታቻና ተቀባይነት ማግኘት፣ እንዲሁም በትምህርት ሂደት ለሚጠበቅ ውጤት ሲባል የሚከናወን ውስኛ ተግባር ነው (Guthrie, Bennett and McGough; No date)። የቀረበን ጽሑፍ ይዞ የራስን ልምድና ተመክሮ በማንጠሪያነት በመጠቀም ከሌላ ወገን (ጸሐፊ) የተላለፈን ሀሳብ በወጉ የመረዳትና እንዳስፈላጊነቱ በተግባርም፣ በነቢብ- በኅሊናም ምላሽ የመስጫና የመግባቢያ ጠቃሚ ክሂል ይበልጥ ጠቃሚና ውጤታማ እንዲሆን በተደጋጋሚ ልምምድ ሊዳብር ይገባዋል (ዓለም፤ 2001፣ Ruddell, 1999, p. 23)።

ስለልምድ ምንነትና አገኛኘቱ ትንሽ ማብራሪያ መጨመር አስፈላጊ ነው፤ ሰው በሕይወት ሂደቱ ውስጥ በሚኖረው ጊዜና ሊያሟላ በሚያስበው ጉዳይ ውጤታማ ለመሆን ተደጋጋሚ ድርጊቶችን ይፈጽማል፤ የድርጊቱ ተደጋጋሚነት እንደሚፈጸመው ሁኔታ ቀላልነት ወይም ከባድነት፣ አለበለዚያም ውስብስብነት ሊወሰን ይችላል። ይሁንና ይህ አንድን ነገር ደጋግሞ የመሥራት፣ የማከናወን ወይም የመፈጸም ተግባር ልምድ ተብሎ ሊወሰድ ይችላል። ደጋግሞ መሥራትን ወይም መፈጸምን ብቻ ሳይሆን ባይሠራ ወይ ባይፈጽም በሰውየው አካልና አእምሮ ላይ አንዳች ቅሬታ ወይም እንከን መፈጠሩ አይቀርም። በየቀኑ የአካል እንቅስቃሴ የሚያደርግ ሰው አንድ ቀን ቢያቋርጥ የአካል መተሳሰርና መፍዘዝ ሊታይበት ይችላል። በየቀኑ ጥዋት ጥዋት አንድ ስኒ ቡና ወይም ማኪያቶ መጠጣትን የዘወትር ተግባሩ ያደረገ ሰው አንድ ቀን ቢተው እንዲሁ በዚያ በተለመደው ሰዓት ላይ ሊያዛጋው ወይም እንቅልፍ እንቅልፍ ሊለው፣ አለበለዚያም እጅግ አድርጎ ሊያቅበጠብጠው ይችላል። የንባብ ልምድን ሱስ እስከመሆን ደረጃ መድረስ በሚመለከት Birhanu, 1999, p. 90[3] Heckschen, (1968) የተባሉ ጸሐፊ ጠቅሶ ‹‹የንባብ ልምድ በሕይወት ሙሉ አብሮ የሚዘልቅና የማይላቀቁት ተግባር ሊባል የሚችል›› መሆኑን አመልክቷል። እዚህ ላይ የሰው የልምድ መከሰቻ

[3] ጥቅሱ በመገኛ ቋንቋው በአባሪነት ተያይዟል።

ወይም መገለጫ ሁኔታዎች ከሰው ወደ ሰው፣ ከሁኔታ ወደ ሁኔታ ሊለያዩ እንደሚችሉ ማስተዋል ይገባል፡፡

በዚህ ቅኝት ውስጥ የተተኮረበት የንባብ ልምድ ይዞታ እንደሁኔታውና እንደሰዉ ፍላጎት ሊለያይ ቢችልም፣ በተለይ በትምህርት ሕይወት ውስጥ ባለፉ ሰዎች ዘንድ በትምህርታቸው መጠንና ባካበቱት እውቀት ልክ የሚወሰን መሠረታዊ የንባብ ልምድ ሊኖራቸው ይገባል የሚል መነሻ የያዘ ነው፡፡ ምክንያቱም ትምህርት ቤቶች ገና ከጅምሩ ከፊደል ቅርጽ መለየት ጀምረው እያደራጁና እየመሩ ተማሪዎቻቸውን (የየግለ ተማሪዎች ክሂሎት መለያየት እንደተጠበቀ ሆኖ) ወደከፍተኛ የንባብ ችሎታ የማሸጋገር ተልእኮ ይወጣሉ ተብሎ ስለሚታሰብ ነው (ሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/ ኢንስቲትዩት 1995፣ 1996)፡፡ በዚህ የትምህርት ቤቶች ተልእኮ ውስጥ ግለሰብ ተማሪዎች በሚኖራቸው የወልና የግል ተሳትፎና ጥረት የንባብ ፍላጎታቸው ዳተኝነት ወይም ንቁነት፣ የተግባራዊ ጥረታቸውና የችሎታቸው ስኬት ወይም ውድቀት በንባብ ችሎታቸው ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድርባቸው ይችላል፡፡ እንዲሁም፣ በሚቀርቡላቸው የመማሪያ መጻሕፍት ጥራት፣ በመምህራኑ የማስተማር ዘዴ ብቃትና የክፍል ውስጥ አተገባበር የተነሳ የችሎታ ደረጃቸው ሊለያይ ይችላል፡፡ ሆኖም ግን እንደቀሰሙት ልምድና ደረጃ፣ ማለትም አራተኛ ክፍልን ያጠናቀቁ ተማሪዎች ስምንተኛ ክፍልን ካጠናቀቁቱ አነስተኛ ችሎታ ሊኖራቸው ይችላል ብሎ መገመት፣ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የቀሰሙ ተማሪዎች በንባብ ልምድ ብርታት ረገድ አንደኛ ደረጃ ካጠናቀቁ ተማሪዎች የተሻለ አቅም፣ ፍላጎትና ችሎታ ይኖራቸዋል የሚል ሀሳብም መሰንዘር ይቻላል፡፡

## የንባብ ልምድ እንዴት ሊዳብር ይችላል?

ከላይ እንደተገለጸው የንባብ ልምድ የሚጀምረው በአመዛኙ በመደበኛ ትምህርት ሂደት ውስጥ ነው፡፡ ልጆች ከሙዓለ ሕጻናት አንስቶ ከፊደል ጋር መተዋወቅና መለማመድ ይጀምራሉ፡፡ የንባብ ልምድ ባለው የሀገሪቱ ሥርዓተ ትምህርት መሠረት በተዘጋጁ መርሆዎች መነሻነት በተሰናዱ የመማሪያና የማስተማሪያ ቁሳቁሶች፣ እንዲሁም የመምህራኑ ሥልጠናና የማስተማር ብቃት እየታገዘ ቀስ በቀስ የሚያድግና ከትምህርት ቤት የሚገኝ ትሩፋት ነው (ዓለም፤ 2001፣ ፈቃደ፤ 1997)፡፡ ይህ ትሩፋት እንደተማሪው ፍላጎትና ትጋት እያደገና እየሰፋ፣ ተማሪው

ከትምህርት ቤት ወጥቶ በሥራ ዓለም ሲሰማራ ደግሞ በግሉ በሚያደርገው ተከታታይ ልምምድ ይበልጥ እየዳበረና የሕይወቱ አንድ አካል እየሆነ የሚሄድ ነው፡፡ የንባብ ልምዱ የዳበረ ግለሰብ ለእለት ተእለት ሥራውና ሕይወቱ የሚያስፈልጉትን መረጃዎች ብቻ ሳይሆን ከሚያነበው ነገር ላይ በመነሳት ሰፊ የማስተዋልና የማመዛዘን፣ ከተለመዱትና ዘወትራዊ ከሆኑት የሕይወቱ ክንዋኔዎች ወደ አዳዲስ ልምዶችና እውቀቶች እንዲሁም ወደ ፈጠራ ሙከራዎች የመሸጋገር ኃይል ሁሉ ይኖረዋል፡፡ የሚከተለውም ጥቅስ ይህንኑ ያስረዳል፤

> የተካነ አንባቢ የቀረበለትን ጽሑፍ መረዳት ብቻ ሳይሆን አስተሳሰቡን ለማስፋፋት ይጠቀምበታል፤ … በንባብ ክሂሎት የመበልጸግ ሂደት ሕይወትን ሙሉ አብሮ የሚጓዝ ነው፡፡ ወደ ተካነ አንባቢነት የሚደረገው ጉዞ ከተለመዱ የሕይወት ተመክሮዎችና ከተካበተ እውቀት ይበልጥ እየረቀቀና እየጠለቀ የሚመራ ሂደት ነው (Reutzel, and Cooter, 1999; p.11)[4]፡፡

ቀደም ብለው የተደረጉ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት የንባብን ችሎታ ለማሳደግና ልምዱን ለማጎልበት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ትምህርት እንደሚቀርብላቸው የታወቀ ነው፡፡ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች፣ በተለያዩ ደረጃዎችና ጊዜዎች የተከናወኑት እነዚህ ጥናቶች የሚያስገነዝቡት የንባብ ትምህርትና ልምምድ በየትምህርት ቤቶቹ የሚከናወኑ ቢሆንም በተማሪዎቹ ላይ ግን ተፈላጊው ችሎታ ወይም ክሂል አለመታየቱን ነው፡፡ ‹‹… ተማሪዎች በደረጃቸው የቀረቡላቸውን የትምህርት ይዘቶች አንብበው የመገንዘብ ችሎታቸው ዝቅተኛ እንደሆነና የመማሪያ ቋንቋው የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብም የሚፈለገውን የንባብ ክሂል ለማዳበር ብቃት እንደሌለው…›› (ወንድአጥር፤ 1993፤ ገጽ፣ 54)፤ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ከዚህና ከሌሎችም ተመሳሳይ ጥናቶች (ጌታቸው፤ 1986፣ በድሉ፤ 1988፣ እንግዳው፤ 1992፣ ተክሉ፤ 1996) መረዳት የሚቻለው ትምህርት ቤቶቻችን በማንኛውም ሁኔታ የንባብ ክሂልና ልምዱ ጎልብቶ የተማሪዎች የቀሪ ሕይወት ችሎታ እንዲሆን አለማድረጋቸውን ነው፡፡ ይኸንን ሀሳብ ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ፣ ማስተዋል (1989)፣

[4] ጥቅሱ በመገኛ ቋንቋው በአባሪነት ተያይዟል፡፡

> … ጥናቱ የሚመለከታቸው ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ያሳያል፤ ለተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ መሆን … የትምህርት አሰጣጥና የመማሪያ መጽሐፉ በዋነኛነት ይጠቀሳሉ፡፡ ከመጠይቅ በተሰበሰቡት መረጃዎች መሠረት ንባብን ከማስተማሪያና ከመማሪያ መጽሐፉ አኳያ ችግሮች አሉ፡፡ በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የንባብ ትምህርት ተማሪዎችን እንደማያሳትፍ፣ አብዛኞቹ ተግባራት በመምህሩ እንደሚከናወኑ፣ ተማሪዎች በቂ ልምምድ እንደማያደርጉ በምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ (ገጽ፣ የለውም)

ሲል አጠቃሏል፡፡

ከላይ እንደተጠቆመው፣ የንባብ ችሎታ የሚገኘውና የሚዳብረው በመሠረቱ በትምህርት ቤቶች ውስጥ መሆኑ ግልጽ ነው፤ ከዚህ አኳያ ሲታይ በማስተዋልና በሌሎቹም አጥኚዎች የተደረሰበት ግኝት በየትምህርት ቤቶቻችን የሚቀርበው የንባብ ክሂል ማዳበሪያ ትምህርትና ልምምድ፣ እሱንም ከግብ ለማድረስ የሚዘጋጁ የመማሪያና ማስተማሪያ መጻሕፍት፣ ተግባራዊ ክንዋኔውን የሚመሩትና የሚያግዙት መምህራን የማስተማር ብቃትና የአቀራረብ መንገድ ሁሉ በሚጠበቀውና በተገቢው አካሄድ ላይ እንዳልሆኑ ያሳያል፡፡ ከነዚህ መጠነኛ ማብራሪያዎችና መንደርደሪያዎች የምናገኘው ተጨባጭ ጥቆማ በየትምህርት ቤቶቻችን በቂ የንባብ ትምህርትና ልምምድ የማይሰጥ መሆኑን፣ የንባብ ፍላጎትን በማነሳሳት ረገድ በቂ መነሻ የሚሆኑ የመማሪያ መጻሕፍት አለመኖራቸውን ነው፡፡ በቂ ትምህርትና ልምምድ ያላገኘ ተማሪ ደግሞ በሥራ ዓለምና በቀሪው ሕይወቱ ሁሉ ከንባብ ከሚገኝ ቁሳዊም ሆነ መንፈሳዊ ጥቅም የተገለለ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም፡፡

ከዚህ በላይ ልዩ ልዩ ልምዶችንና የጥናት ውጤቶችን ከንድፈ ሀሳባዊ መንደርደሪያዎች ጋር አጣምሮ፣ በቀረበው ክለሳ ድርሳን መሠረት በመግቢያው የተጠቆሙትን የጥናት ዓላማና ዝርዝር ጥያቄዎች ይዞ፣ መጠይቅ ተሰናድቶ፣ ተበትኖና ተሰብስቦ የተገኘው የቅኝት መረጃ እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

## መረጃ ትንተና

መጠይቁ ከፊል ዝግና ክፍት የሆኑ 14 ዋና ዋና ጥያቄዎችን ይዟል[5]፡፡ ከፊል ዝግ የተባሉት መላሹ መጠነኛ ጥረት በማድረግ አጫጭር መልሶችን የሚሰጥባቸው ናቸው፤ ምሳሌ፣ ጥ. 2፡፡ ክፍት የሆኑት ደግሞ መላሹ ሙሉ በሙሉ አሳቡንና ልምዱን እንደሚፈልገው እንዲጽፍ እድል የሚሰጡትን ነው፤ ምሳሌ፣ ጥ.11፡፡ ለእነዚህ 14 ጥያቄዎች የተሰጡት ምላሾች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

በመጠይቁ ላይ መጀመሪያ የቀረበው ጥያቄ መጠይቁን የሞሉ ሰዎችን ማንነት ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ለማግኘት የሚረዳ ነው፡፡ የጥያቄውም ዓላማ የመላሾችን የልምድ ስብጥርና ደረጃ ለመረዳት ነው፡፡

### ሰንጠረዥ 1፡- መጠይቁን የሞሉ ሰዎች ግላዊ መረጃ

| 1.1. እድሜ | | 1.2. ፆታ | | 1.3. የት/ ደረጃ | | 1.4. የሥራ መስክ | | 1.5. የሥራ ምድብ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መጠን | ብዛት | ሴ | ወ | ደረጃ | ብዛት | ዓይነት | ብዛት | ዓይነት | ብዛት |
| 15-20 | 3 | 29 | 45 | 1ኛ | - | ተማሪ | 4 | ትምህርት | 4 |
| 21-25 | 8 | | | 2ኛ | 20 | የግል ሠ. | 21 | ተራ ሠራተኛ[6] | 42 |
| 26-30 | 19 | | | ኮሌጅ ዲ | 30 | የመን. ሠ. | 40 | ኃላፊ | 20 |
| 31-35 | 11 | | | ቢ.ኤ. | 16 | መያድ | 4 | ያልገለጹ | 8 |
| 36-40 | 8 | | | ኤም ኤ | 6 | ጡረታ | 1 | | |
| 41-45 | 6 | | | ፒኤች ዲ | 0 | ያልገለጹ | 4 | | |
| 46-50 | 7 | | | ያልገለጹ | 1 | | | | |
| 51-55 | 7 | | | | | | | | |
| 56-60 | 0 | | | | | | | | |
| 61-65 | 2 | | | | | | | | |
| 66+ | 0 | | | | | | | | |
| ድምር | 74 | 74 | | | 74 | | 74 | | 74 |

[5] ይህን መጠይቅ ለመሙላት ፈቃደኛ የሆኑልኝን ግለሰቦች በሙሉ፣ እንዲሁም መጠይቁ የያዛቸው ጥያቄዎች ተገቢ መሆናቸውን ፕሮፌ. ሀብታሙ ወንድሙ፣ ረ/ፕሮፌ. ዓለም እሸቱና ረ/ፕሮፌ. ጌታቸው እንዳላማው አንብበው አስተካክለውልኛልና ሁሉንም ከልብ አመሰግናቸዋለሁ፡፡

[6] ተራ ሠራተኛ ማለት በሚሠራበት መ/ቤት በኃላፊነት ወይም በአለቃነት የማያገለግልን ሰው የሚመለከት ነው፡፡

በሰንጠረዥ 1 ላይ ለማየት እንደሚቻለው መጠይቁን የሞሉ ሰዎች እድሜ ከ15 እስከ 65 የሚደርስ ነው፡፡ እንደሚታወቀው እድሜ ዋነኛ የልምድ ማካበቻ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ይህን መጠይቅ የሞሉ ሰዎች አብዛኞቹ ከ26 -30 (በቁ.19 (25.68%) ናቸው፤ ከነሱ ቀጥለው የሚገኙት 31-35 (በቁ.11 (14.87%) ሲሆኑ በሦስተኛ ደረጃ የሚገኙት 21 -25 እና 36 -40 ያሉት (በቁ. 8 (10.8% ለእያንዳንዳቸው) ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በእያንዳንዱ የእድሜ ክልል መጠነኛ ብዛት ያላቸው መላሾች ይገኛሉ (56-60፣ 66+ በስተቀር) ፡፡

በፆታም ረገድ 29 (39.2%) ሴቶች፣ 45 (60.8%) ወንዶች መጠይቁን ሞልተዋል፡፡ ይህም መረጃ መጠይቁን የሞሉት ወገኖች በአንድ ፆታ ላይ ብቻ ያተኮረ አስተሳሰብና ልምድ ያልቀረበበት መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በትምህርት ደረጃም በኩል ሲታይ ሁለተኛ ደረጃን ያጠናቀቁ 20 (27.02%)፣ የኮሌጅ ዲፕሎማ ያላቸው 30 (40.54%)፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ደግሞ 16 (21.62%) ሲሆኑ ሁለተኛ ዲግሪ እንዳላቸው የገለጹት 6 (8.11%) ናቸው፡፡ በሥራ መስክ በኩል የግል ተቀጣሪዎች 21 (28.38%)፣ 40 (54.05%) የሆኑት የመንግሥት ሠራተኞች ናቸው፡፡ በሥራ ኃላፊነት በኩል የተገኙት መረጃዎች ደግሞ መጠይቁን ከሞሉት ሰዎች ውስጥ አብዛኞቹ ተራ ሠራተኞች 42 (56.76%)፣ በኃላፊነት ደረጃ (የሥራ መሪ) ደግሞ የሚገኙት 20 (27.02%) መሆናቸው ተጠቁሟል፡፡ ትምህርት፣ የሥራ መስክና ኃላፊነት ለንባብ ልምዳችን መጎልበትም ሆነ መዳከም የየበኩላቸውን በጎ ወይም አፍራሽ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ መሆናቸው በግልጽ የሚታወቅ ጉዳይ ነው፡ ፡ በዚህ መሠረት ከጠቅላላ መላሾች 61 (82.43%) የሚሆኑት በመንግሥትም ሆነ በግል መሥሪያ ቤቶች የሚሠሩ ናቸው፡፡ በንባብ ልምድ ረገድ አነሰም አደገ ከት/ቤት አንጻች ትሩፋት ያገኙ መሆናቸውን መገመት አያዳግትም፡፡

እዚህ ላይ፣ በዚህ የልምድ ቅኝት ትኩረት የተደረገበት የትንታኔ አካሄድ የመላሾቹን ድምር መልስ የሚመረኮዝ እንጂ በጾታ፣ በእድሜና በመኖሪያ አካባቢ ወይም በሥራ ልምድ አማካይነት በሚገኙ የተለያዩ ፍላጎቶችና ተመክሮዎች ከሚያሳድሯቸው ተጽእኖዎች አንጻር አለመሆኑን በቅድሚያ መጠቆም ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ ቀጥሎ በሚገኘው ሰንጠረዥ ላይ በ4 ንዑሳን ክፍሎች ተዘርዝረው የቀረቡት ጥያቄዎች አጠቃላይ የንባብ ልምድ መሠረት የጣለበትንና እያደገ የሄደበትን እውነታ ለመገንዘብ ያስችላሉ ተብለው ነው፡፡

## ሰንጠረዥ 2፡- የትምህርት ቤት የንባብ ልምድ

| ጥ.ቁ. | የጥያቄው ይዘት | የመላሽ ብዛት | | | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | % | የለም | % | ብ. | % |
| 2.1. | በትምህርት ቤት ቆይታ በክፍል ውስጥ የሚሰጥ የንባብ ልምምድ ነበር? | 70 | 94.59 | 4 | 5.41 | 74 | 100 |
| 2.2. | መልስዎ ‹አዎ› ከሆነ የሚያነብቡዋቸው መጻሕፍት | | | | | | |
| | - የመማሪያ | 8 | 24.32 | | | | |
| | - ተጨማሪ | 18 | 124.32 | | | | |
| | - ሁለቱንም | 27 | 36.49 | | | 63 | 85.14 |
| | - መልስ ያልሰጡ | 11 | 14.86 | | | 11 | 14.86 |

የንባብ ልምድ የሚጀምረው ባብዛኛው በትምህርት ቤት መሆኑ ይታወቃል፡፡ አንድ ተማሪ (ሕፃን) ከፊደል ጋር መተዋወቅ ሲጀምር አብሮ ተግባራዊ የሚሆንና በሂደት እያደገ የሚገኝ ዓይነተኛ የእውቀት ማግኛ መንገድ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች በተማሪዎቻቸው ዘንድ የንባብ ልምድ ይዳብር ዘንድ ከፍተኛውን ኃላፊነት የሚወስዱ መሆናቸው ይታመናል- በተለይ እንደእኛ ባለ ትምህርት በኅብረተሰቡ ውስጥ ባልተስፋፋበት እውነታ ውስጥ፡፡ ይህንኑ ከግምት በማስገባት መጠይቁን የሞሉ ሰዎች ይኸንኑ የንባብ ልምምድ በትምህርት ቤት አግኝተው እንደሆነ ተጠይቀው (በሰንጠረዥ 2 በጥ.2.1. እንደተመለከተው) 70 (94.59%) የሚሆኑት የሰጡት ምላሽ አዎንታዊ ነው፡፡ ከዚያ ቀጥሎ በ2.2. ላይ ለቀረበላቸውና የሚያነቡዋቸውን መጻሕፍት ዓይነት እንዲጠቁሙ ለሚጠይቀው የሰጡት ምላሽ 18 (24.32%) የመማሪያ መጽሐፋቸውን፣ ከመማሪያ መጽሐፍ ውጪ የሚያነቡ 18 (24.32%)፣ ሁለቱንም ዓይነት መጻሕፍት እናነብ ነበር ያሉት ደግሞ 27 (36.49%) ናቸው፡፡[7]

እዚህ ላይ ተማሪዎች የሚማሩበትን መጽሐፍ የማንበባቸው ጉዳይ ብዙም የሚያነጋግር አለመሆኑን ማስተዋል ይገባል፡፡ ምክንያቱም በትምህርቱ ሂደት ፈተና ለማለፍም ሆነ ከክፍል ወደ ክፍል ለመሻጋገር የሚፈልግ ተማሪ ቢያንስ፣ ቢያንስ

---

[7] በዚህና በሌሎቹም ተከታታይ ሰንጠረዦች አልፎ አልፎ የመልሶቹን ቁጥር ከጠቅላላ መላሾች አንጻር ስንመለከተው ልዩነት እንዳለ እንረዳለን፤ ይህ የሆነው መላሾች ከአንድ በላይ መልስ የመስጠት እድል ስላላቸው ነው፡፡

የመማሪያ መጽሐፉን የማንበብ ግዴታ አለበትና ነው፡፡ ከንባብ ልምድ መጎልበት አኳያ መታየት ያለበት ከመማሪያ መጻሕፍት ውጪ የሚደረግ በአመዛኙ የግል ጥረትንና ተነሳሽነትን ተመርኩዞ እውቀትንና ልምድን ለማሳደግ የሚደረግ ሕይወትን ሙሉ አብሮ የሚዘልቅን እንቅስቃሴ የሚመለከት መሆን አለበት፡፡ በዚህ ረገድ የመላሾቹ ልምድ የሚጠበቀውን ያህል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ከላይ የቀረበው ሀሳብ ተከታይ ጥያቄ ደግሞ በትምህርት ቤት ቆይታቸው ከክፍል ውጪ እንዲያነቡ የሚያበረታታ ሁኔታ መኖሩን ለማወቅ የቀረበ ነበር፡፡ ለዚህና ለተከታዩ ጥያቄ የሰጡዋቸው መልሶች ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ቀርበዋል፡፡

**ሰንጠረዥ 3፡- ከክፍል ውጪ ለማንበብ አበረታች ሁኔታ መኖር**

| ጥ.ቁ. | የጥያቄው ይዘት | የመላሽ ብዛት | | | | ጠ.ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | % | የለም | % | |
| 2.3. | ከክፍል ውጪ እንዲያነብቡ ይበረታቱ ነበር? | 68 | 91.89 | 6 | 8.11 | 74 (100%) |
| 2.4. | መልስዎ ‹አዎ› ከሆነ የሚያበረታቱዎት፤ | | | | | |
| | - መምህራን | 36 | 48.65 | | | |
| | - ወላጆች | 36 | 48.65 | | | |
| | - ጓደኞች | 25 | 33.78 | | | |
| | - የግል ተነሳሽነት | 48 | 64.86 | | | |
| | - ሌላ | 3 | 4.05 | | | |

መላሾች ከክፍል ውጪ እንዲያነብቡ ይበረታቱ እንደነበር ሀሳብ እንዲሰጡ ተጠይቀው 68 (91.89%) የሆኑት የሰጡት መልስ አዎንታዊና አበረታች ሁኔታች ተሟልተውላቸው የነበር መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ከላይ መማሪያ መጻሕፍትንና ከነሱም ውጪ እናነብ ነበር ካሉት መላሾች አኳያ ሲታይ ይህ ለ2.3. ጥያቄ የሰጡት መልስ ተጣጣሚነት ያለው ይመስላል፡፡

ቀጥሎ በጥ.2.4. ላይ ለቀረበውና የአበረታች ሁኔታዎችን ምንነት እንዲጠቁሙ ለተጠየቀው የሰጡት መልስ የግል ተነሳሽነትን 48 (64.86%) በመስጠት ያስቀድሙና የመምህራንንና የወላጆችን ድርሻ ለእያንዳንዳቸው 36 (48.65%) ነጥብ በመስጠት በሁለተኛ ደረጃ ያስቀምጧቸዋል፡፡ የጓደኞች ተፅእኖ ደግሞ 25

(33.78%) በማግኘት በሦስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ለዚህኛው ጥያቄ የተሰጠው መልስ ምንም እንኩዋ በትምህርት ቤት አበረታች ሁኔታዎች መኖራቸውን የሚጠቁም ቢሆን ለግል ተነሳሽነት ቅድሚያ የሚሰጥ ሆኖ ተገኝቱዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳው ነገር ከላይ በክለሳ ድርሳኑ ውስጥ ያነሳነውን ሀሳብ፣ ንባብ የግል ጥረትንና ትጋትን የሚጠይቅ፣ በአመዛኙም ተግባሩ ግለኝነትን የተመረኮዘ መሆኑን እንደሚያረጋግጥልን ፍንጭ መስጠቱ ነው፡፡ ንባብን በማበረታታት ረገድ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ትምህርት ቤቶች (መምህራን) መሆናቸው በልዩ ልዩ ምርምሮች የተረጋገጠ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ የወላጆች ሚና እንደሚጎላም ይታመናል፡፡ ይህ አመኔታ በዚህ መጠይቅ ሀሳባቸውን በሰጡ ሰዎች ዘንድ እንዳልሰራ ማስተዋል ይቻላል፡፡

በልዩ ልዩ የሕይወት ዘርፍ፣ በተለይ ትምህርት ነክ ጉዳዮች ላይ የጉዋደኞች ተጽዕኖም በእጅጉ ተፈታታኝ መሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም በነዚህ መላሾች ዘንድ በሦስተኛ ደረጃ ላይ መገኘቱ ምናልባት ሌላ የጥናት ፈር ያመላክት ይሆን? የሚል ጥያቄ ይጭራል፡፡

ከዚህ ቀጥሎ የቀረበው ጥያቄ መላሾቹ ከትምህርት ቤት ከወጡና በሥራ ዓለም ከተሰማሩ በኋላ በትምህርት ቤት ያገኙትን የንባብ ልምምድ ገፍተውበት እንደሆነ ለማወቅ የሚያስችል ዓላማ ያለው ነው፡፡

## ሰንጠረዥ 4፡- በሥራ ዓለም (ከትምህርት ቤት ከወጡ በሁዋላ) ያለዎት የንባብ ልምድና መገለጫው

| ጥ. ቁ. | የጥያቄው ይዘት | የመላሽ ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % |
| 3. | - ሁል ጊዜ አነባለሁ<br>- አልፎ አልፎ አነባለሁ<br>- ፈጽሞ አላነብም | 30<br>44<br>0 | 40.54<br>59.46<br>0.0 |
| | **ድምር** | **74** | **100.00** |
| 4. | የንባብ ልምድዎ በአማካይ እንዴት ይገለጻል?<br>- በሳምንት አንድ መጽሐፍ<br>- በወር አንድ መጽሐፍ<br>- በወር ሁለት መጽሐፎች<br>- በአገኘሁት አጋጣሚ<br>- መልስ ያልሰጡ | <br>12<br>34<br>7<br>7<br>14 | <br>16.22<br>45.95<br>9.46<br>9.46<br>18.91 |
| | **ድምር** | **74** | **100.00** |

ለቀረበው ጥያቄ (3) የተሰጠው መልስ አብዛኞቹ 44 (59.46%) አልፎ አልፎ እንደሚያነብቡ፣ 30 (40.54%) ሆኑት ደግሞ ሁል ጊዜ የሚያነብቡ መሆናቸውን ያሳያል። ይህ እውነት ቀደም ሲል ከተጠቀሰው ከBirhanu (ገጽ 106) ግኝት ጋር ይጣጣማል። ይህን ሁል ጊዜም ሆነ አልፎ አልፎ የማንበብ ልምድ በተግባር እንዴት ሊገለጥ እንደሚችል ለማወቅ የንባብ ልምድዎ በአማካይ እንዴት ይገለጻል የሚል ጥያቄ (4) ቀርቦ ነበር።

ለጥያቄ 4 ከተሰጠው ምላሽ እንደምናየው ብዙዎቹ 34 (45.95%) የሚሆኑት በወር አንድ መጽሐፍ የሚያነቡ ናቸው። በሳምንት አንድ መጽሐፍ የሚያነብቡት 12 (16.22%) ብቻ ናቸው። በሁለት ወር አንድ መጽሐፍና በአጋጣሚ የሚያነቡት ደግሞ በተመሳሳይ ሁኔታ 7 (9.46%) ብቻ መሆናቸው ይታያል። ቀሪዎቹ 14 (18.91%) ያህል መላሾች ልምዳቸውን አልጠቆሙም።

የንባብ ልምድን ለማወቅ ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠውን መልስ ከላይኛው ‹‹ሁል ጊዜ አነባለሁ›› ለሚለው ጥያቄ ከሰጡት መልስ ጋር ማስተያየት ያስፈልጋል። በመሆኑም 30 (40.54%) መላሾች ሁል ጊዜ እንደሚያነቡ ከገለጹ በኋላ በሳምንት አንድ መጽሐፍ የሚያነቡት ብዛት 12 (16.22%) መሆኑ በሁለቱ መልሶች መካከል መፋለስ እንዳለ ወይም አንድ መጽሐፍ ለማንበብ ከሳምንት በላይ የሚፈጅባቸው መላሾች መኖራቸውን ማስተዋል ይቻላል። ቀደም ሲል በተደረገ ጥናትም (ዓለም፤ 2001) በማንበብ ፍላጎትና በተግባራዊ ክንዋኔው መካከል ልዩነት መኖሩ ተጠቁሟል።

ቀጥሎ የቀረበው ጥያቄ ይዘት መላሾቹ አዘውትረው የሚያነቧቸውን መጻሕፍት፣ መጽሔቶችና ጋዜጦችን እንዲጠቁሙ እድል የሚሰጥ ነበር። ይህ ጥያቄ በውስጡ ሰባት ያህል ንዑሳን ሀሳቦችን በተናጠል የሚያነሳ ሆኖ የቀረበ ነው። መላሾች እርግጥ ከላይ እንደጠቆሙት ሁልጊዜም ሆነ አልፎ አልፎ የሚያነቡ መሆናቸውን ለማመሳከርም የሚረዳ ነው።

## ሰንጠረዥ 5፡- የሚያነቧቸው መጻሕፍት፣ መጽሔቶችና ጋዜጦች

| ጥ.ቁ. | የጥያቄ ይዘት | የመላሽ ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 5.1. | ወጥ የፈጠራ ሥራዎች | | |
| | - ረጃጅም ልቦለዶች | 51 | 68.92 |
| | - አጫጭር ልቦለዶች | 44 | 59.46 |
| | - የግጥም መጻሕፍት | 27 | 36.49 |
| | - የተውኔት መጻሕፍት | 8 | 10.81 |
| | - ሌሎች | 0 | 0.0 |

የመጠይቁ መላሾች የሚያነቧቸውን የፈጠራ ሥራዎች በዓይነት ለይተው እንዲጠቁሙ ለቀረበው ጥያቄ የሰጡት መልስ ከላይ እንደተመዘገበው ቀርቧል፡፡ ከመላሾቹ ውስጥ አብዛኞቹ ረጃጅምና አጫጭር ልቦለዶችን (51፣ 68.92%፣ 44፣ 59.46%) እንደሚያነቡ ገልጸዋል፡፡ በግጥም ረገድ 27 (36.49%) መላሾች እንደሚያነቡ ሲጠቁሙ የተውኔት መጻሕፍት የሚያነቡት ግን 8 (10.81%) ብቻ እንደሆኑ ከሰንጠረዡ ማየት ይቻላል፡፡ የተውኔት አንባቢዎች ቁጥር አነስተኛ ሆኖ መገኘት ምናልባት ተውኔት በመድረክ የሚታይ በመሆኑ ምክንያትና ታትመው የሚገኙ የተውኔት ሥራዎች ብዙም ስላልሆኑ ይሆን? ያሰኛል፡፡

ከዚህ ቀጥሎ የቀረበው ንዑስ ጥያቄ መላሾች ካነበቧቸው መጻሕፍት ውስጥ ይበልጥ የሚያስታውሱዋቸውን እንዲጠቁሙ የሚያደርግ ነበር፡፡ በዚሁ መሠረት አብዛኞቹ መላሾች በተደጋጋሚ የጠቆሙዋቸውን በቅደም ተከተል እናቀርባለን፡፡

**ሰንጠረዥ 6፡- አንባቢዎች ይበልጥ የሚያስታውሷቸውና የጠቆሙዋቸው መጻሕፍት**

| ጥ. ቁ. | የመጽሐፍ ርእስ | ያንባቢ ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 5.2. | ይበልጥ የሚያስታውሷቸው መጻሐፍት፣ | | |
| | ረጃጅም ልቦለዶች፤ | | |
| | - ፍቅር እስከ መቃብር | 34 | 45.95 |
| | - ኦሮማይ | 12 | 16.22 |
| | - የልምዣት | 10 | 13.51 |
| | - ሰመመን | 9 | 12.16 |
| | - ወንጀለኛው ዳኛ | 8 | 10.81 |
| | - ቆንጆዎቹ | 7 | 9.46 |
| | - ከአድማስ ባሻገር | 6 | 8.11 |
| | - ከቡስካ በስተጀርባ | 5 | 6.76 |
| | - የታንጉት ምስጢር | 5 | 6.76 |
| | - ሀዲስ | 4 | 5.41 |
| | አጭር ልቦለድ | | |
| | - በራሪ ቅጠሎች | 5 | 6.76 |
| | ግጥሞች | | |
| | - እሳት ወይ አበባ | 6 | 8.11 |
| | - ኗሪ አልባ ጎጆዎች | 3 | 4.05 |
| | ተውኔት | | |
| | - ሀሁ በስድስት ወር | 1 | 1.35 |
| | - የከርሞ ሰው | 1 | 1.35 |

በዚህ ዝርዝር መሠረት የአንባቢዎችን ምርጫና የጠቆሙዋቸውን መጻሕፍት ብዛትና ዓይነት ስንመለከት በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ተደጋግመው ከሚጠቀሱት አንጋፋና ወጣት ደራሲዎች መካከል የጥቂቶችን እናገኛለን፡፡ በተለይ በረጅም ልቦለድ ዘርፍ የበርካታ ደራሲዎች *ሥራዎች* ተጠቁመዋል፡፡ *ፍቅር እስከ መቃብርን*[8] 34(45.95%)፣ *ኦሮማይን* 12 (16.22%) *የልምዣትን* 10 (13.51%) በተከታታይ አስርና ከዚያ በላይ ሰዎች ጠቁመዋቸው እናገኛለን፡፡ በአጫጭር ልቦለዶች ዘርፍ ግን አንድ መጽሐፍ ብቻ ነው ስሙ ተጠርቶ የምናገኘው- *በራሪ*

[8] Concher 1970, ባደረገው ጥናት በወቅቱ በተጠኚዎች በቀዳሚነት የተመረጡት የአቤ ጉበኛ መጻሕፍት ነበሩ፡፡ ቀደም ሲል የተጠቀሰው የብርሃኑ ጥናት ግኝት ደግሞ ከአሁኑ ጥናት ጋር ይስማማል፡፡

*ቅጠሎች*፡፡ (በሰንጠረዥ 5 ላይ 44 (59.46%) የሚሆኑት አጫጭር ልቦለዶች እንደሚያነቡ መግለጻቸውን ይዘን በርእስ ደረጃ አስታውሰው የጠቀሱት አንድን መጽሐፍ ብቻ መሆኑን ስናስተውል ‹‹ለምን›› የሚል ሌላ ጥያቄ የሚጭር ይመስላል፡፡)

የንባብ ልምድ ፍተሻው ሁሉንም የጽሑፍ ዘሮች የሚመለከት እንደመሆኑ መጠን የሚቀጥለው ጥያቄ ያተኮረው በኢልቦለዶች ዘርፍ የመላሾችን ልምድ በመቃኘት ላይ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የሚከተለውን ዝርዝር እናገኛለን፡፡

**ሰንጠረዥ 7፡- የምታነቧቸው የኢልቦለድ መጻሕፍት እና ይበልጥ የሚያስታውሱት**

| ጥ.ቁ. | የጥያቄ ይዘት | የመላሽ ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 5.3. | የኢልቦለድ (ፈጠራ ይልሆኑ) መጻሕፍት | | |
| | - የታሪክ መጻሕፍት | 47 | 63.51 |
| | - ልዩ ልዩ (ጠቅላላ) እውቀቶች | 46 | 62.16 |
| | - ከግል ሥራ (ሙያ) ጋር የተገናኙ | 26 | 35.14 |
| | - የሕይወት ታሪክ | 23 | 31.08 |
| 5.4. | ከኢልቦለዶች ውስጥ ይበልጥ የሚያስታውሱት | | |
| | - አጠቃላይ የኢትዮጵያ ታሪክ | 13 | 17.57 |
| | - አጼ ቴዎድሮስ | 6 | 8.11 |
| | - አጼ ምኒልክ | 4 | 5.41 |
| | - ሃይማኖት ነክ መጻሐፍት | 4 | 5.41 |
| | - የሃያኛው ክ.ዘ. ኢትዮጵያ ታሪክ | 3 | 4.05 |
| | **ድምር** | **30** | **40.54** |

በኢልቦለድ መጻሕፍት ዘርፍ አብዛኞቹ መላሾች የሚያነቧቸው መጻሕፍት የታሪክ 47 (63.51%)፣ ልዩ ልዩ (ጠቅላላ) እውቀቶች 45 (62.16%) መሆናቸውን ማስተዋል ይቻላል፡፡ በሰንጠረዥ 1 ላይ እንደተመለከትነው ከጠቅላላ መላሾች 65 ያህሉ በልዩ ልዩ የሥራ መስክ የተሰማሩ ናቸው፡፡ ከዚህ አኳዋያ በሥራቸው ምክንያት ለሙያ ድጋፍ እና ለጠቅላላ እውቀት መበልጸግ እንዲያግዙዋቸው የታሪክ፣ የጠቅላላና የሙያ መጻሕፍት ተመራጭ እንደሆኑ መገመት ይቻላል፡፡

በሕይወት ታሪክ ዘርፍም በኩል ቢሆን የአንባቢዎች ፍላጎት እንዳለ ፍንጭ የሚሰጥ ነው- ቢያንስ ከመላሾቹ ሲሶ ያህል 23 (31.08%) ምርጫቸው እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

እንደፈጠራ ሥራዎች ሁሉ በዚህም የኢልቦለድ ዘርፍ አብዛኞ መላሾች ምርጫቸውን እንደሚከተለው አመልክተዋል፡፡ ከጠቅላላ የመጠይቁ መላሾች ውስጥ፣ ከኢልቦለድ መጻሕፍት ውስጥ ያነበቧቸውን አስታውሰው የጠቀሱት 30 (40.54%) ብቻ ናቸው፡፡ ሌሎቹ አልጠቀሙም፡፡ እነዚህ መላሾች ከሚያነቧቸው መጻሕፍት ውስጥ ይበልጡን ቁጥር የሚይዙት ኢትዮጵያን የሚመለከቱ ጠቅላላ የታሪክ መጻሕፍት መሆናቸውን ማስተዋል ይቻላል፡፡ በሰንጠረዥ 7 ላይ እንደምንመለከተው መላሾቹ የሚያነቧቸው መጻሕፍት የታሪክ ብቻ ሳይሆኑ ሥራ (ሙያ) ጠቀስ ጭምር መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡ በዚሁ ሰንጠረዥ በተራ ቁጥር 5.4. ላይ ግን ይህ የልምድ ግጥምጥነት አይታይም፡፡

በግል ሁኔታም ሆነ ከአካባቢ ተጨባጭ እውነታ አንጻር መላሾች የሚያነቧቸው መጻሕፍት ወጥ የሆኑ የፈጠራና የኢልቦለድ መጻሕፍት ብቻ አይደሉም፡፡ በፈጠራም ሆነ በልዩ ልዩ ርእስ ጉዳዮች ላይ የተጻፉ ልቦለድና ኢልቦለድ መጻሕፍትን ከልዩ ልዩ ቋንቋዎች ተተርጉመው ሲገኙ ማንበብ የተለመደ ነው፡፡ በዚህ በኩል ለውን የንባብ ልምድ አንድ ገጽታ ለማወቅ ሲባል የሚከተለው ጥያቄ ቀርቦ ነበር፡፡

**ሰንጠረዥ 8:- የሚያነቧቸውና ይበልጥ የሚያስታውሷቸቸው የትርጉም መጻሕፍት**

| ጥ. ቁ. | የጥያቄ ይዘት | የመላሾች ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 5.5. | የሚያነቧቸው የትርጉም መጻሕፍት | | |
| | - የፈጠራ ሥራዎች ትርጉም | 43 | 58.11 |
| | - የኢልቦለድ ሥራዎች ትርጉም | 22 | 29.73 |
| | **ድምር** | **65** | **87.84** |
| 5.6. | ይበልጥ የሚያስታውሷቸውን ይጠቁሙ | | |
| | - ሳቤላ | 12 | 16.22 |
| | - ብርቅርቅታ | 10 | 13.51 |
| | - ብቀላ | 3 | 4.05 |
| | - ምንዱባን | 2 | 2.70 |
| | - እፎይታ | 2 | 2.70 |
| | - የፍርድ ቀን ዘመቻ | 2 | 2.70 |
| | - ነገም ሌላ ቀን ነው | 2 | 2.70 |
| | **ድምር** | **33** | **44.59** |

ከምላሹ እንደምንመለከተው 43 (58.11%) የሚሆኑት ልምዳቸው ፈጠራ የሆኑ ትርጉሞችን እንደሚያነቡ ሲያሳይ 22 (29.73%) የሆኑት ደግሞ የኢልቦለድ ትርጉሞችን የሚያነቡ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የቀረበው ጥያቄ ደግሞ ከሚያነቧቸው ውስጥ ይበልጥ የሚያስታውሷቸውን እንዲጠቁሙ እድል የሚሰጥ ነበር፡፡

በሰንጠረዥ 8 ላይ እንደምንመለከተው የፈጠራም ሆኑ የትርጉም መጻሕፍት እናነባለን ያሉት ከጠቅላላ መለሾች ውስጥ 65 (87.84%) ናቸው፡፡ እነዚሁ አንባቢዎች ይበልጥ የሚያስታውሷቸውን የትርጉም መጻሕፍት እንዲጠቁሙ ለተጠየቀው ጥያቄ 33 (44.60%) ብቻ ናቸው መልስ የሰጡት፡፡ በመላሾች ይበልጥ የተጠቆሙት *ሳቤላና ብርቅርቅታ* የተሰኙ የትርጉም መጻሕፍት መሆናቸውን ልብ ይሏል፡፡

የንባብ ሁኔታ ሲነሳ ትኩረቱ በመጻሕፍት ላይ ብቻ እንዳልሆነ ይታወቃል፡፡ ይልቁንም የእለት ተእለት ውሎዎችንና የአካባቢንም ሆነ የዓለምን ሁኔታ ለመረዳት በቅርብ የሚገኙ ጋዜቶችንና መጽሔቶችን ማንበብ የማይታለፍ የአንባቢ ተግባር ነው፡፡ተከታዩ ጥያቄም መላሾች አዘውትረው የሚያነቧቸውን መጽሔቶችና ጋዜጦች ዘርዝሩ የሚል ነበር፡፡ በዚህ መሠረት የተገኘው መረጃ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

**ሰንጠረዥ 9፡- አዘውትረው የሚያነቧቸው መጽሔቶችና ጋዜጦች**

| ጥ.ቁ. | ጋዜጦች | የመ. በዛት | % | መጽሔቶች | የመ. ብዛት | % |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5.7 | - አዲስ አድማስ | 38 | 51.35 | - ቁም ነገር | 10 | 13.51 |
| | - ሪፖርተር | 27 | 36.49 | - ቃል ኪዳን | 9 | 12.16 |
| | - አዲስ ነገር | 17 | 22.98 | - ጽጌረዳ | 7 | 9.46 |
| | - አዲስ ዘመን | 16 | 21.62 | - ሮዝ | 6 | 8.11 |
| | - ሜዲካል | 9 | 12.16 | - ዘመን | 6 | 8.11 |

መላሾች አዘውትረው ከሚያነቧቸው ጋዜጦችና መጽሔቶች ውስጥ በተደጋጋሚ የጠቀሷቸው ከላይ በሰንጠረዥ 9 የተዘረዘሩት ናቸው፡፡ እንደሚታየው ከተዘረዘሩት ጋዜጦች ውስጥ ላቅ ባለ ቁጥር የተጠቀሰው *አዲስ አድማስ* 38 (51.35%) ነው፡፡ ዝቅተኛው *ሜዲካል* 9 (12.16%) ነው፡፡ ከመጽሔቶች ደግሞ *ቁም ነገር* 10

(13.51%) በማግኘት ሻል ያለ አንባቢ እንዳለው ሲታይ *ሮገና ዘመን መጽሔቶች* እያንዳንዳቸው 6 (8.11%) አንባቢዎች አሉዋቸው።

ከላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች የተሰጡት መልሶች እንደሚጠቁሙን መጠይቁን የሞሉ ሰዎች ልቦለዶችንም ሆነ ኢልቦለዶች መጻሕፍት ያነባሉ፤ ጋዜጦችንና መጽሔቶችን እንደ መጻሕፍቱም ባይሆን ዘርዝረዋል። ይሁንና ከየት ከየት እንደሚያገኟቸው ወይም በምን መንገድ እጃቸው እየገቡ እንደሚያነቧቸው እንዲገልጹ ተጠይቀው ነበር። በዚህ ረገድ የተሰጠውን ምላሽ በሚከተለው ሰንጠረዥ እንይ፤

**ሰንጠረዥ 10፡-የሚነበቡ መጻሕፍትን፣ ጋዜጦችንና መጽሔቶችን ከየት ያገኛሉ?**

| ጥ.ቁ. | መጻሕፍት | መ.ብ | % | ጥ.ቁ | ጋዜጣና መጽሔት | መ.ብ | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 6.1 | በግዢ | 50 | 67.57 | 6.2 | በግዢ | 63 | 85.14 |
| | ከግለሰብ በውሰት | 44 | 59.46 | | ከግለሰብ በውሰት | 30 | 40.54 |
| | ከቤተ መጻሕፍት | 40 | 54.05 | | ከቤተ መጻሕፍት | 18 | 24.32 |
| | በኪራይ | 16 | 21.62 | | በኪራይ | 10 | 13.51 |

ከመጠይቁ የተገኘው መረጃ መላሾች ከአንድ በላይ ምንጭ እንዳላቸው ያሳያል። ከላይ የቀረቡት ምንጮች የሚነበቡ መጻሕፍት፣ ጋዜጦችና መጽሔቶች ከየት እንደሚያገኙ በመጠይቁ ላይ በጉልህ ይቅረቡ እንጂ ሌሎች የማግኛ ምንጮችም ተጠቁመዋል። እነሱም ስጦታ፣ ፎቶ ኮፒ፣ ኢንተር ኔት፣ መስሪያ ቤት፣ የውበት ሳሎን የመሳሰሉት ሁሉ በጥቂት መላሾች ተጠቁመዋል።

መጻሕፍትንም ሆነ ጋዜጦችንና መጽሔቶችን ከግለሰብ በመዋስ፣ ከቤተ መጻሕፍት በማውጣት፣ በግዢና በኪራይ እያገኙ ማንበብ የተለመደ ተግባር ነው። በዚህ ዓይነት መጠይቁን የሞሉ ሰዎች የሚያነቡዋቸውን ነገሮች ከየት እንደሚያገኙ ሲጠቁሙ፣ መጻሕፍትን 50 (67.57%) በግዢ፣ 44 (59.46%) በውሰት፣ 40 (54.05%) ከቤተ መጻሕፍትና 16 (21.62%) በኪራይ እንደሚያገኙ ገልጸዋል። በጋዜጦችና መጽሔቶችን በሚመለከት ደግሞ 63 (85.14%) በግዢ፣ 30 (40.54%) ከግለሰብ በውሰት፣ ከቤተ መጻሕፍት በማውጣት 18 (24.32%) እና 10 (13.51%) በኪራይ (በመሳሰሉት መንገዶች ባንዱ ወይ በሌላው እየተጠቀሙ) እንደሚያገኙ ጠቁመዋል።

ከዚህ ከቀረበው ዝርዝር እንደሚታየው የመጠይቁ መላሾች የሚያነቧቸውን መጻሕፍትንም ሆነ ጋዜጣና መጽሔቶችን በግዢ ያገኛሉ፡፡ መጻሕፍትን የሚዋሱትን ያህል ግን ጋዜጦችን አይዋሱም፤ ለዚህም ይመስላል ጋዜጦችና መጽሔቶች ገዢዎች ቁጥራቸው ከፍ ብሎ የታየው፡፡

መጻሕፍትን፣ ጋዜጦችንና መጽሔቶችን በልዩ ልዩ መንገድ እያገኙ የሚያነቡ መላሾች የመኖራቸውን ያህል ጥቂቶች ደግሞ እንደማያነቡ ገልጸዋል፡፡ ላለማንበባቸው ምክንያታቸውን እንዲገልጹ ለቀረበው ጥያቄ በዛ ያሉ መላሾች የሰጡት መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

## ሰንጠረዥ 11፡- የማያነቡ ቢሆን ምክንያትዎን ይግለጹ

| ጥ.ቁ. | የጥያቄው ይዘት | የመላሾች ብዛት | |
|---|---|---|---|
| ጥ. 7 | የማያነቡበት ምክንያት | የመ. ብዛት | % |
| | - መጻሕፍት ስለማያገኙ | 8 | 10.81 |
| | - የመጻሕፍት ዋጋ ውድነት | 7 | 9.46 |
| | - የጊዜ ማጣት/ሥራ ብዛት | 20 | 27.03 |
| | - የማንበቢያ ሥፍራ ማጣት | 14 | 18.92 |
| | - መልስ ያልሰጡ | 25 | 33.78 |
| ድምር | | 74 | 100.00 |

በመጠይቁ መላሾች መሠረት ማንበብን የሚያደናቅፉ ወይም የሚገቱ ዋና ዋና ችግሮች በሰንጠረዡ ተጠቁመዋል፡፡ ጊዜ ማጣት/ ሥራ መብዛት 20 (27.03%) በማግኘት ቀዳሚ ችግር ነው፡፡ የማንበቢያ ሥፍራ ማጣት ደግሞ ተከታዩ ችግር ነው 14- (18.92%)፡፡ መጻሕፍት አለማግኘትና የዋጋ ጉዳይ ግን ከሁለቱ አንጻር ሲታዩ ችግርነታቸው መለስተኛ ነው፡፡ መልስ ያልሰጡ ደግሞ 25 (33.78%) ናቸው፡፡

ብዙውን ጊዜ አንድ ሰው በትምህርትም ሆነ በመደበኛ ሥራ ላይ ሲሰማራ ሙሉ ጊዜውን እንዳለ አሟጦ በሥራ ላይ እንደማያውል ይታወቃል፡፡ ከመደበኛ ተግባሩ ውጪ ልዩ ልዩ ለኑሮው ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮችን የማከናወኛ ጊዜያት አሉት፡፡ በቀን ውስጥ በሥራና በጠቃሚ ጉዳዮች ማከናወኛ ላይ ከሚያጠፋቸው ጊዜያት የሚተርፉ ሰዓታት አሉት፡፡ እነዚህን ትርፍ ጊዜያት በምን በምን ድርጊቶች ላይ

እንደሚያሳልፉዋቸው እንዲጠቁሙ ለመጠይቁ መላሾች ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር፡፡ የሰጡትም መልስ እንደሚከተለው ተጠቃልሎ ቀርቧል፡፡

### ሰንጠረዥ 12፡- የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ

| ጥ.ቁ. | የጥያቄ ይዘት | የመላሾች ብዛት (%) | |
|---|---|---|---|
| 8. | ከሥራ ውጪ ያለዎትን ትርፍ ጊዜ በምን በምን ተግባር ላይ ያሳልፋሉ? | | |
| | - መጻሕፍት በማንበብ | 44 | 59.46 |
| | - ፊልም በማየት | 28 | 37.84 |
| | - ከጉዋደኛ ጋር ጭውውት | 15 | 20.27 |
| | - ማኅበራዊ ጉዳዮች መፈጸም | 14 | 18.92 |
| | - ከቤተሰብ ጋር መጫዋወት | 13 | 17.57 |
| | - በትምህርት ላይ | 11 | 14.86 |
| | - ቴሌቪዥንና ራዲዮ መከታተል | 10 | 13.51 |
| | - ትያትር ማየት | 9 | 12.16 |
| | - ቤተክርስቲያን | 6 | 8.11 |
| | - ሙዚቃ ማዳመጥ | 5 | 6.76 |

መላሾች ከመደበኛ የሥራ ማከናወኛ ውጪ ያሉዋቸውን ትርፍ ጊዜያት የሚያሳልፉባቸውን 10 ያህል የጊዜ ማሳለፊያዎችን ጠቁመዋል፡፡ ከላይ በዝርዝሩ ላይ እንደሚታየው ከሁሉም ቅድሚያ የተሰጠው መጻሕፍትን ማንበብ 44 (59.46%) የሚለው ነው፡፡ ከሱ ቀጥሎ የሚመጣው ፊልም ማየት 28 (37.84%)[9]፣ ከጉዋደኛ ጋር ጭውውት 15 (20.27%) እያለ እየቀነሰ ሔዶ ዝቅተኛ መላሾች የጠቆሙት ሙዚቃ ማዳመጥ 5 (6.76%) መሆኑን እናያለን፡፡ ባጠቃላይ ማኅበራዊ ጉዳዮችን መፈጸም፣ ከቤተሰብ ጋር ጭውውት፣ በትምህርት ላይ ማተኮር፣ ቴሌቪዥንና ራዲዮ ማዳመጥ፣ ትያትር ማየትና ቤተክርስቲያን መሄድ እንደጊዜ ማሳላፊያ የሚቆጠሩ ናቸው፡፡

በየእለት ውሏችን አንዳንድ የምንፈልጋቸውን ነገሮች ለመፈጸም በምናደርገው እንቅስቃሴ ላይ አካባቢያችን ተጽዕኖ እንደሚያደርግብን ይታወቃል፡፡ ይህ የአካባቢ (የመኖሪያም ሆነ የሥራ ቦታ) ተጽዕኖ በንባብ ልምድ ላይ ያለውን ድርሻ ለመረዳት

[9] በዓለም እሸቱ (2001) ጥናት ውስጥ ፊልም ማየት ከንባብ ቀድሞ ይገኛል፡፡

የሚያስችል ጥያቄ ቀርቦ መላሾች ያቀረቡት ዝርዝር ሲታይ የሚከተለውን ገጽታ ያሳያል፡፡

**ሰንጠረዥ 13፡- በአካባቢዎ ንባብን የሚበረታታ/ የሚያደናቅፍ ምን ሁኔታ አለ?**

| ጥ.ቁ | የጥያቄ ይዘት | | | የጥያቄ ይዘት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 9. | አበረታች ሁኔታዎች | መ.ብ | % | አደናቃፊ ሁኔታዎች | መ.ብ | % |
| | - ጋዜጣና መጽሔት በብዛት መገኘት<br>- መጻሕፍት ማግኘት<br>- መጻሕፍት መከራየት<br>- መጻሕፍት የመግዛት አቅም መኖር<br>- የቤተሰብ ድጋፍ | 8<br>5<br>3<br>2<br>2 | 10.81<br>6.76<br>4.05<br>2.70<br>2.70 | - የሕዝብ ቤ.መጻሕፍት በአካባቢ አለመኖር<br>- የማንበቢያ ቦታ አለመመቻቸት<br>- የሥራ ጫና<br>- የጎረቤት ጫጫታ<br>- የመጠጥ ቤት ብዛት<br>- ቴሌቪዥን<br>- የቪዲዮ ቤቶች ብዛት<br>- መጻሕፍት አለማግኘት<br>- የዋጋ ውድነት<br>- የፊልም ተጽዕኖ | 14<br>10<br>9<br>5<br>6<br>4<br>3<br>3<br>3<br>3 | 18.02<br>13.51<br>12.16<br>6.76<br>8.11<br>5.41<br>4.05<br>4.05<br>4.05<br>4.05 |

ለጥያቄ ዘጠኝ በተሰጠው የመላሾች መረጃ መሠረት ንባብን ከሚያበረታቱ አካባቢዎችና ሁኔታዎች ይልቅ የሚያደናቅፉት የሚያይሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በአደናቃፊነት የተዘረዘሩት ባንድነት ሲደመሩ 60 (81.08%) ሲሆኑ በደጋፊነት የተመዘገቡት ደግሞ 20 (27.03%) ናቸው፡፡ ይህም አካባቢ በመላሾቹ የንባብ ልምድ ላይ ምን ያህል አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳለው በጉልህ ያሳያል፡፡ ይኸው ነጥብም በአለም (2001) ጥናት ውስጥ ተጠቁሞአል፡፡

ከላይ ከሰንጠረዡ እንደምናየው ልዩ ልዩ ችግሮችና እንቅፋቶች ቢያጋጥሟ ቸውም፣ ደረጃቸውም ቢለያይ መጻሕፍትን የሚያነቡ ሰዎች አሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች መጻሕፍት እንዴት አግኝተው እንደሚያነቡ የመረጃ ምንጫቸውን እንዲጠቁሙ ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ነው፡፡

## ሰንጠረዥ 14፡- መጻሕፍትን ለማግኘት የመረጃ ምንጭዎ

| ጥ.ቁ. | የጥያቄ ይዘት | የመላሾች ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 10 | መጻሕፍትን ለማግኘት የመረጃ ምንጭ | | |
| | - መጻሕፍት መደብር በመሄድ | 38 | 51.35 |
| | - ጓደኛ በመጠየቅ | 36 | 48.65 |
| | - ከጋዜጣ/ መጽሔት አስተያየት በማንበብ | 23 | 31.08 |
| | - ከቴሌቪዥን ማስታወቂያ በማየት | 15 | 20.27 |
| | - ከጋዜጣ/ መጽሔት ማስታወቂያ በማንበብ | 12 | 16.22 |
| | - ከራዲዮ ማስታወቂያ በማዳመጥ | 10 | 13.51 |

በዘመናዊ የግብይት ሥርዓት ውስጥ አንድን ምርት በስፋት ለማዳረስና ተጠቃሚ ለመሆን በልዩ ልዩ መንገድ ማስተዋወቅ የተለመደ አሠራር ነው፡፡ በየእለቱ በጥቅም ላይ ከሚውሉ ቁሳቁሶች ጀምሮ ለዘለቄታው የሚያገለግሉ እቃዎች፣ ምርቶችና ጥበባዊ ውጤቶች ሁሉ ይተዋወቃሉ፡፡ በዚሁ ዓይነት በአገራችን መጻሕፍትን፣ መጽሔቶችንና ጋዜጦችን ማስተዋወቅ ልማድ እየሆነ መጥቷል፡፡ በመሆኑም አንድ ተጠቃሚ ስለአንድ ምርት በልዩ ልዩ መንገዶች (ከአንድ በላይ መንገዶች) ተጠቅሞ መረጃ እንደሚያገኝ የሚጠበቅ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን መጠይቅ የሞሉ ሰዎች በየትኛው ወይም በየትኞቹ መንገዶች ተጠቅመውና መረጃ አግኝተው ስለመጻሕፍት እንደሚያውቁ ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ ከላይ በሰንጠረዥ 14 ቀርቧል፡፡

በዚህ ምላሽ መሠረት 38 (51.35%) የሚያህሉት ከመጻሕፍት መደብር፣ 36 (48.65%) ያህሉ ደግሞ ከጓደኛቸው መረጃ ያገኛሉ፡፡ በመጽሔትና በጋዜጦች ላይ የሚወጡ አስተያየቶችም መጻሕፍትን ለማገኘት በመረጃ ምንጭነት እንደሚያገለግሉ 23 (31.08%) የሆኑት መላሾች ጠቁመዋል፡፡ 15 (20. 27%) የሚሆኑት መላሾች ደግሞ በቴሌቪዥን የሚተላለፍ ማስታወቂያ ማየት የመረጃ ምንጫቸው እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ የጋዜጣ/የመጽሔት እና የራዲዮ ማስታወቂያዎች በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆን መጻሕፍትን ለማግኘት እንደመረጃ ምንጭነት እንደሚያገለግሉ ከተሰጡት መልሶች ለማየት ይቻላል፡፡

ከዚህ በላይ ስለንባብ ልምድ፣ ስለሚነበቡ መጻሕፍት፣ ጋዜጦችና መጽሔቶች የማግኛ ዘዴና የመረጃ ምንጮች፣ እንዲሁም ንባብን ስለሚያበረታቱና ስለሚያደናቅፉ ሁኔታዎችና አካባቢዎች ትንታኔ ቀርቧል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ

የንባብ ልምድ (ባህል) እንዲዳብርና እንዲጎለብት ምን ቢደረግ ይሻላል? የሚል ጥያቄ ቀርቦ የሚከተለው ምላሽ ተገኝቷል፤

### ሰንጠረዥ 15፡- የንባብ ባህል እንዲዳብር ምን ይደረግ?

| ጥ.ቁ. | የጥያቄ ይዘት | የመላሽ ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 11 | የንባብ ባህል እንዲዳብር ምን ይደረግ? | | |
| | - በየአካባቢው ቤተ መጻሕፍት መክፈት | 33 | 44.60 |
| | - የመጻሕፍት ዋጋ መቀነስ | 19 | 25.68 |
| | - ት/ቤቶች ልጆችን የንባብ ትምህርት ያስተምሩ | 9 | 12.16 |
| | - ሕጻናትን ከሥር ጀምሮ ማበረታታት | 8 | 10.81 |
| | - ስለንባብ ጥቅም ቅስቀሳ | 7 | 9.46 |
| | - በንባብ ላይ የልምድ ልውውጥ/ውይይት | 4 | 5.41 |
| | - በልዩ ልዩ እውቀቶች ላይ መጻሕፍት ማቅረብ | 4 | 5.41 |
| | - የመጻሕፍትን ጥራት መጠበቅ | 4 | 5.41 |

የንባብ ልምድ ጎልብቶ በባህልነት እንዲቀጥል ከተፈለገ በየመኖሪያ አካባቢው አመቺ በሆነ ቦታ ሁሉ የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት ማቋቋም እንደሚገባ 33 (44.60%) የመጠይቁ መላሾች ተጠቁሞአል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የሚመጣው ደጋፊ ሀሳብ 19 (25.68%) የመጻሕፍት መሸጫ ዋጋ ይቀንስ የሚለው ነው፡፡ ምንም እንኳ አነስተኛ ጠቋሚ ቢኖራቸው በትምህርት ቤቶች የንባብ ትምህርት ማስተማር፣ ሕጻናት ከሥር ጀምሮ ይበረታቱ፣ ስለንባብ ቅስቀሳ ይደረግ፣ በንባብ ላይ የልምድ ልውውጥ/ ውይይት ይደረግ በልዩ ልዩ እውቀቶች ላይ የተሰናዱ መጻሕፍት ይቅረቡ እና የመጻሕፍት ጥራት ይጠበቅ የሚሉ ሀሳቦች ተሰንዝረዋል፡፡ እነዚህ የመፍትሄ ሀሳቦች ቀደም ሲል የተደረገውን የአለም እሸቱን ግኝት የሚያጠናክሩና የሚደግፉ ናቸው፡፡

የንባብ ልምድ እንዲጎለብት የልዩ ልዩ ተቋማትን ተሳትፎ መጠየቁም ይታወቃል፤ በዚህ ረገድ የንባብ ልምድ ለማዳበር የጎላ ድርሻ ይኖራቸዋል በማለት የሚከተሉት ቀርበው በደረጃ እንዲያስቀምጧቸው ተጠይቆ ነበር፡፡

## ሰንጠረዥ 16፡- የንባብ ልምድን ለማዳበር የባለድርሻ አካላት ዝርዝር

| ጥ.ቁ. | የባለድርሻ አካላት ዝርዝር | ደረጃ | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 |
| 12 | - ት/ቤቶች | 30 | 24 | 5 | 3 | 1 | - | - | 1 | - |
| | - ወላጆች | 30 | 10 | 1 | 2 | 2 | - | - | - | 2 |
| | - የት/ቢሮዎች | 6 | 2 | 6 | 7 | 8 | 12 | 7 | 3 | - |
| | - በት/ልማት የተሰማሩ | 7 | - | 6 | 7 | 8 | 8 | 6 | 3 | 2 |
| | - ደራሲዎች | 17 | 3 | 8 | 7 | 10 | 2 | 8 | 1 | 2 |
| | - መገናኛ ብዙኃን | 11 | 6 | 15 | 13 | 2 | 3 | 1 | 3 | 1 |
| | - አሳታሚ ድርጅቶች | 7 | 2 | 1 | 3 | 3 | 5 | 3 | 18 | 2 |
| | - ማተሚያ ድርጅቶች | 5 | - | 2 | 1 | 3 | 1 | 3 | 4 | 21 |
| | - የባህል ቢሮዎች | 4 | 1 | 3 | 1 | 6 | 8 | 11 | 3 | 3 |

መላሾች ከአንደኛ እስከዘጠነኛ ደረጃ እንዲመድቡ በተሰጠው እድል መሠረት ለእያንዳንዱ ባለድርሻ አካል የጠቀሜታውን ወይም የቅድምናውን ደረጃ አሲዘዋል፤ የንባብን ልምድ (ባህል) ለማዳበርና ለማጎልበት ቅድሚያ የተሰጣቸው ባለድርሻ አካላት (በአንደኛ ደረጃ የተጠቀሱት 30፣ 30) ትምህርት ቤቶችና ወላጆች ናቸው፡፡ በዚሁ ረድፍ ደራሲዎች 17 በቁጥር በማግኘት ይጠቀሳሉ፤ መገናኛ ብዙኃን ደግሞ በቁጥር 11 አግኝተው ተጠቁመዋል፡፡ ማተሚያ ቤቶችን አብዛኞቹ መላሾች (በቁጥር 21 የሚሆኑት) በመጨረሻው ደረጃ (9ኛ) ላይ ያስቀምጧቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ፣ የንባብ ባህልን የሕዝብ ባህል በማድረግ ረገድ ጉልህ እርምጃ የታየው ከማተሚያ ቤቶችና ከትምህርት ቤቶች መስፋፋት ጋር ተያይዞ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ የሌሎቹን ድርሻና ደረጃ ከሰንጠረዡ ማየትና ማሰላሰል ይቻላል፡፡

መላሾች የባለድርሻ አካላትን መዘርዘር ብቻ ሳሆን የተሳትፎ (የኃላፊነት) ደረጃም እንዲያመለክቱና ተጨማሪ ሀሳብ እንዲያቀርቡ ለሚጋብዙት ነጻ ጥያቄዎች (ጥ.13 እና 14.) የሰጡት መልስ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### ሰንጠረዥ 17፡- ነጻና ተጨማሪ አስተያዬት

| ጥ.ቁ | ነጻና ተጨማሪ አስተያዬቶች | የመላሽ ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 13፣14 | - በመገናኛ ብዙኃን ተከታታይ ውይይትና ቅስቀሳ፣ | 38 | 51.35 |
| | - ተማሪዎች እንዲያነቡ የት/ቤቶች ተከታታይ ግፊትና ማበረታቻ፣ | 23 | 31.08 |
| | - ወላጆች በማንበብ ረገድ ምሳሌ መሆንና ለልጆቻቸው መጻሕፍት መሸለም፣ | 22 | 29.73 |
| | - በመኖሪያ አካባቢዎች የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት ማቋቋም፣ | 16 | 21.62 |
| | - የመጻሕፍትን የኅትመትና ያቀራረብ ጥራት መጠበቅ፣ | 14 | 18.92 |
| | - በት/ቤቶች ራሱን የቻለ የማንበቢያ ጊዜ መመደብ፣ | 5 | 6.76 |

በክለሳ ድርሳኑ ውስጥ እንደተጠቆመው፣ የንባብ ልምድ መሠረት የሚጣለው በትምህርት ቤት ውስጥ ነው፡፡ በትምህርት ቤትም የተጣለውን መሠረት በልዩ ልዩ ወገኖችና ተቋማት ድጋፍ ማጎልበትና ማበርታት ያስፈልጋል፤ ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ 17 ላይ እንደሚታየው፣ የንባብ ባህልን በማድበር ረገድ ባለድርሻ አካላት እንዴት ሊሳተፉ እንደሚችሉ በመጠይቁ ለቀረቡት ጥ.13 እና 14 መላሾች ነጻና ተጨማሪ አስተያየት ሰጥተዋል፡፡ በዚህም መሠረት የንባብን ልምድ በማጎልበት ረገድ ጉልህ ድርሻ ሊኖራቸው ከሚገቡት ውስጥ መገናኛ ብዙኃን 38 (51.35%)፣ የትምህርት ቤቶች ግፊትና ማበረታቻ 23 (31.08%)፣ የወላጆች ምሳሌነትና ግፊት 22 (29.73%)፣ በመኖሪያ አካባቢዎች የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት መቋቋም 16 (21.62%) የመጻሕፍት ኅትመትና ያቀራረብ ጥራት መጠበቅ 14 (18.92%) እና በትምህርት ቤቶች ራሱን የቻለ የንባብ ክፍለ ጊዜ መመደብ 5 (6.76%) የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡

### ማጠቃለያና የመፍትሔ ሀሳቦች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የንባብ ልምድ ይዞታን መመርመር መሆኑ በቅኝቱ መግቢያ ውስጥ ተገልጾአል፡፡ በቅኝቱ የሚመለሱ ዝርዝር ጥያቄዎችም እንዲሁ ተጠቁመዋል፡፡ እነሱን መሠረት በማድረግ 14 ዝርዝር ጥያቄዎችን የያዘ መጠይቅ

ተዘጋጅቶ አዲስ አበባ ውስጥ በልዩ ልዩ አካባቢዎች ማለትም በመዝናኛ ሥፍራዎች፣ በመሥሪያ ቤቶችና በመኖሪያ አካባቢዎች ለመቶ ሰዎች ተሰጥቷል። ከመቶው መጠይቅም 74 ተመልሷል። ከተመለሰው መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ቀደም ባሉት ገጾች በቀረቡ 17 ሰንጠረዦች ላይ በየወገናቸው ተመድበው ተተንትነዋል። በመጠይቁ ውስጥ እንደቀረበው የጥያቄ ዓይነትና ይዘትም በክለሳ ድርሳናችን ውስጥ በተደረገው ንድፈ ሀሳባዊ ሀተታ መሠረት ተተንትነዋል። ከትንታኔውም የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች በማጠቃለያነት ማቅረብ ይቻላል።

## የማጠቃለያ ነጥቦች

- የንባብ መሠረት የሚጣለው በተማሪው የትምህርት ቤት እድሜ ላይ መሆኑ ይታወቃል(ሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/ ኢንስቲትዩት 1995፣ 1996)። በዚህ መሠረት የዚህ ቅኝት ግኝት የሚጠቁመው ትምህርት ቤቶች ተፈላጊውን ልምድና ፍላጎት መሠረት አለማስያዛቸውን ነው።
- የንባብ ልምድ ይጎለብት ዘንድ ትምህርት ቤቶች በጥቅሉ ይጠሩ እንጂ በግልጽ የሚጠቀሱት መምህራንና የመማሪያ መጻሕፍት ናቸው። እነዚህ ሁለቱ ዋነኛ ተጠሪዎች የንባብን ልምድ መሠረት በማስያዝ ረገድ ብዙም ተጽእኖ እንዳላሳደሩ ለየጥያቄዎቹ የተሰጡት መልሶች ጠቁመዋል።
- አብዛኞቹ መላሾች 44 (59.46%) ከመደበኛ ሥራቸው ውጪ ያላቸውን ጊዜ በማንበብ እንደሚያሳልፉ መግለጻቸው ተደጋፊ ቢሆንም የሥራ ብዛት፣ የማንበቢያ ቦታ ማጣት፣ የሚነበቡ መጻሕፍት ዋጋ ውድነት፣ የመሳሰሉትን በንባብ አደናቃፊነት ዘርዝረዋል።
- በሚነበቡ ነገሮች ዓይነትም በኩል ልቦለዶች፣ ኢልቦለዶች፣ ወጥ ሥራና ትርጉሞች፣ ጋዜጦችና መጽሔቶች እንደሆኑ ተጠቁመዋል።
- ስለመጻሕፍት አዳዲስ መረጃዎችን ለማግኘትና ገዝተው ወይም ተውሰው ለማንበብ ሲፈልጉ መረጃ የሚገኙት ከመጻሕፍት መደብሮች፣ ከጓደኞች፣ በጋዜጣና በመጽሔት እንዲሁም በራዲዮና በቴሌቪዥን ከሚሰራጩ ማስታወቂያዎችና ከሚታተሙ የመጻሕፍት አስተያየቶች እንደሆነ ጠቁመዋል።
- በአንድ ሰው ዘለቄታዊ ሕይወት ውስጥ የንባብን ልምድ ለማጎልበት የሥራም ሆነ የመኖሪያ አካባቢ አስተዋጽዖ እንዳላቸው እውነት መሆኑን ይህ ቅኝት ጾታና እድሜ ሳይለይ አመልክቷል።

## የመፍትሔ ሀሳቦች

በዚህ ጥናት ግኝት መሠረት የንባብ ልምድን አጎልብቶ የዘወትር ተጠቃሚ ለመሆን ልዩ ልዩ ሁኔታዎች እንዲሟሉ ያስፈልጋል፡፡ እነሱም፤

- የንባብ ልምድ መሠረት የሚጣለው በትምህርት ቤቶች ውስጥ በመሆኑ በዚህ በኩል፣ በመምህራን ሥልጠና፣ በመማሪያ ማስተማሪያ ቁሳቁስ ጥራትና አቅርቦት ላይ፣ በክፍል ውስጥ ለንባብ ራሱን የቻለ መርሀ-ግብር በመዘርጋት ረገድ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በየትምህርት ቤቶች ተማሪዎች በግል ተነሳሽነት ሊያነቡባቸው የሚችሉ ቤተ መጻሕፍትንና የማንበቢያ ቦታዎችን በማመቻቸት በኩል ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ወገኖች ማለትም ከትምህርት ሚኒስቴርና ከየክልሉ ትምህርት ቢሮዎችና መምህራን አሠልጣኝ ተቋማት፣ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ተግባራዊ ምላሽ ይጠበቃል፡፡
- የንባብ ልምዱ የጎለበተ ትውልድ ለማፍራት ቀዳሚ ተጠቃሹ ትምህርት ቤት ቢሆንም ወላጆችም ልምዱ ሥር ሰዶ፣ ልጆች በኋላም ጎልማሶች የሕይወታቸው ሙሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የበኩላቸውን ድርሻ ሊወጡ ይገባል፤ ልጆች ምን እንደሚያነቡ፣ እንዴት እንደሚያነቡ መከታተል ብቻ ሳይሆን ራሳቸውም እያነበቡ ለልጆቻቸው አብነት እንዲሆኑ መትጋት እንደሚያስፈልጋቸው በቅኝቱ ከተገኙ መረጃዎች ላይ ተነስቶ ማሳሰብ ተገቢ ነው፡፡
- የንባብ ልምድ እንዲጎለብትና በጎ ባህል እንዲሆን የጎላ ሚና ከሚጫወቱት ውስጥ መገናኛ ብዙኃን ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ጋዜጦችና መጽሔቶች የመጻሕፍት አምድ በመክፈት ተከታታይ መረጃዎች ሊያትሙ፣ ራዲዮና ቴሌቪዥን እንዲሁ ከመጻሕፍት ዓለም የመሳሰሉ መርሀ-ግብሮችን ሊዘረጉና ሰፊ ውይይትና ቅስቀሳ የሚያደርጉበትን ስልት ሊያሰናዱ ይገባቸዋል፡፡
- ንባብ ዘላቂ የሕይወት ክሂሎት የሚሆነው ሁሉም የተማረ ወገን እንደልምድና ባህል አድርጎ ሲይዘው በመሆኑ በመኖሪያ አካባቢዎችና በመስሪያ ቤቶች ውስጥ መጻሕፍት የሚገኙባቸውን ሥፍራዎች

(ቤተ መጻሕፍት፣ የንባብ ቤቶች) ማዘጋጀት የየአካባቢዎቹ መሪዎች፣ አስተዳዳሪዎች ሁሉ እንዲተጉበት ያስፈልጋል፡፡

- የንባብ ጉዳይ የሚጠቅሳቸው ደራሲዎች፣ የሥነ ጽሑፍ ተመራማሪዎች፣ የሙያ ማኅበራትና የንባብ ክበባት የውይይትና የሂስ መድረኮች በማዘጋጀት፣ በልዩ ልዩ ጋዜጦችና መጽሔቶች፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን የሚሠራጩ መጣጥፎችን በማሰናዳት ብርቱ ቅስቀሳና ያላሰለሰ ጉትጎታ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- የዚህ ጥናት የትኩረት በታና የተጠኝዎች ብዛት እጅግ ውስን ነው፡፡ በዚህ መነሻነት ግን ሰፋ ባለ ቦታና በርከት ባሉ ተጠኝዎች ላይ በማለም ሰፊና ጥልቅ ጥናት ማካሄድ እንደሚገባ የዚህ ቅኝት የማጠቃለያ ነጥቦችና የመፍትሄ ሀሳቦች ጠቋሚዎች መሆናቸውን ማስተዋል ይገባል፡፡

## ማመሳከሪያዎች


ማስተዋል ውበቱ፤ (1989) *የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ፡- በአዲስ አበባ በሚገኙ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት፡፡* አዲስ አበባ፤ አ.አ.ዩ ድህረ ምረቃ ት/ቤት፡፡

ምሕረቱ ጴ. ጉታ፤ (1999) **የንባብ ባሕልና ቤተ ክርስቲያን፡፡** አዲስ አበባ፤ የኤስ ኣይ ኤም ሥነ ጽሑፍ፡፡

ሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/ ኢንስቲትዩት፤ (1995) *ከ1ኛ - 4ኛ ክፍሎች አጥጋቢ የመማር ክህሎት*፤ አዲስ አበባ፤ (*ያልታተመ*)፡፡

ሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/ ኢንስቲትዩት፤ (1996) *በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ክፍሎች (ከ5ኛ - 8ኛ) በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚጠበቅ አጥጋቢ ብቃት፡፡* አዲስ አበባ፤ (*ልታተመ*)፡፡

በድሉ ዋቅጅራ፤ (1988) *ተሳታፊነት-ጭምትነት የሰብእና ዓይነት ከድርሰት መጻፍና አንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ፤ በሦስት ኮሌጆች ተማሪዎች ላይ የተደረገ ጥናት።* አዲስ አበባ፤ አ.አ.ዩ ድህረ ምረቃ ት/ቤት።

ተክሉ ዕቋር፤ (1996) *በዘጠነኛ ክፍል የንባብ ትምህርት አቀራረብ ትንተና፡- መንግሥታዊ በሆኑና መንግሥታዊ ባልሆኑ የአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ላይ ያተኮረ ጥናት።* አዲስ አበባ፤ አ.አ.ዩ ድህረ ምረቃ ት/ቤት።

ታዬ አየለ፤ (1997) *በአዲስ አበባ መስተዳደር ትምህርት ቢሮ በ1990 ዓ.ም. በተዘጋጀው የስድስተኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ።* አዲስ አበባ፤ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት ለአርት ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት።

ንጉሥ ወዳጅነው፤ (1993) *በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ለአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መጻሕፍት ውስጥ የምንባብ አመራረጥ ትንታኔ ከተማሪዎች ፍላጎት አንፃር፣ በሁለት ት/ቤቶች የተካሄደ ጥናት።* አዲስ አበባ፤ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት ለአርት ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት።

አብዮታዊ ዴሞክራሲ ጋዜጣ፤ (1988) *የዘመናችን የህትመት ሁኔታ ሲቃኝ፡* ኅዳር 27-ታህሳስ 3 በ6ኛ ዓመት ቁ. 140ኛ እትም፤ ገጽ 7።

አያልነህ ሙላት፤ (1985) *ደራስያንን ለማፍራትና ለማበረታታት ምን መደረግ አለበት?* ለነፃ የመጻሕፍት ገበያ ኮንፈረንስ የቀረበ፤ አዲስ አበባ ግንቦት 1985 (ተባዝቶ የተጠረዘ)።

እንግዳው ዘውዴ፤ (1992) *የ‹ቶፕ ዳወን (Top Down)› የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ተግባራዊነትና ውጤታማነት በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት።* አዲስ አበባ፤ አ.አ.ዩ ድህረ ምረቃ ት/ቤት።

ወንድአጥር ደነቀ፤ (1993) *በማስተማሪያ ቋንቋነት በኦሮሚያ ክልል ለአራተኛ ክፍል የተዘጋጀ የአማርኛ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ተገቢነት።* አዲስ አበባ፤ አ.አ.ዩ ድህረ ምረቃ ት/ቤት።

ዓለም እሸቱ፤ (2001) *የወጣቶች የንባብ ልምድ ፍተሻ በአዲስ አበባ ወጣቶች መነሻነት፡ ፡ መድበለ ጉባዔ፤-የምእተ ዓመቱ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እድገት የንባብ ባህል ይዞታና የመጪው ክፍለ ዘመን ፈር፡* አርታኢ፣ ደረጀ ገብሬ፤ አዲስ አበባ፤ የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር ኅትመት (ገጽ 60 - 79)።

ደረጀ ደስታ፤ (1986) *መጽሐፍ ያልያዘ ትውልድ። አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ እለተ ሰንበት አምድ፡* ግንቦት 21 ቀን በ54ኛ ዓመት ቁ. 220ኛ እትም፤ ገጽ 2።

ጋሻው መሀመድ፤ (1995) *በአማራ ብ/ክ/መንግሥት ትምህርት ቢሮ ታትመው በማገልገል ላይ ባሉት በ7ኛና በ8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተመረጡት ምንባቦች የተማሪዎችን የንባብ ተነሳሽነት ለመፍጠር ብቃት አላቸው?* አዲስ አበባ፤ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት ለአርት ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት።

ጌታቸው አዱኛ፤ (1986) *ለአሥረኛ ክፍል የተመረጡ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦች የብቃት ደረጃ።* አዲስ አበባ፤ አ.አ.ዩ ድህረ ምረቃ ት/ቤት።

ፈቃደ አዘዘ፤ (1997) *ቁዘማ፡- የንባብ ጉዳይ በኢትዮጵያ፤* ‹መጻሕፍት ለኢትዮጵያ የፓናል ውይይት ስለ መጽሐፍ ንባብ በኢትዮጵያ› በሚል ርእስ ለሚካሄድ የሙሉቀን ጉባዔ የተዘጋጀ ጽሑፍ፤ ቅዳሜ ሚያዝያ 15 ቀን 1997 ግዮን ሆቴል፣ አዲስ አበባ።

Birhanu Tefera. (1999). *Leisure Reading and Readership of Books: With Reference to some Literate Group in Bahir Dar.* **Ethiopian Journal of Language and Literature**; No. 9, Institute of Language Studies; AAU Printing Press, 1999.

Concher, J.R.H. (1970). *An Initial Readership Survey of Ethiopia.* Addis Ababa; (Memeographed).

Davies, F. (1995). **Introducing Reading**. London: Penguin Books Ltd.

Greellet, F. (1981). **Developing Reading Skills**. Cambridge: Cambridge University Press.

Guthrie, J. T., Lois B. & McGoug, K. (No date). *Concept-Oriented Reading Instruction: An Integrated Curriculum to Develop Motivations and Strategies for Reading.* http://www.teach.virginia.edu/go/clic/nrrc/cori_r10.html

Reutzel, D. and Cooter, R. (1999). **Balanced Reading Strategies and Practices.** New Jersey: Merrill, an imprint of Prentice Hall.

Ruddell, M. Rapp. (1999). **Teaching Content Reading and Writing**. 2nd ed. New York: John Wiley & Sons, Inc.

Tamene Kitila. (1992). *A Preliminary Survey of the Reading Interests of Addis Ababa University Students.* **The Ethiopian Journal of Education.** Institute of Educational Research; Addis Ababa University, PP. 47 – 77.

Zikri, L. B. (1986). *Reading Habits of Adults in Egyp*t. Paper prepared for presentation at the World Congress on Reading, International Reading Association, London, England.

**አባሪ:- ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው**

3. Reading can be a habit and, in like manner is thus long-lasting and gripping like addiction.
4. The skilled reader not only understands print, but uses print to support and extend thinking. … The process of becoming skilled in reading is a lifelong journey. The journey to skilled reading involves processing print that is further and further removed from one's own experiences and knowledge.